# የመምህሩ መምሪያ

## የዘመነ መጽሐፍ ቅዱስ ደረጃ 1 እና 2

ተከታታይ ትምህርቶች 1-6

www.besweb.com

## የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርቶች አገልግሎት

በሕግ የተመዘገበ የዩናይትድ ኪንግደም ለጋሽ ድርጅት (የምዝገባ ቁጥር 1096157)

**ተልእኮ**

በአለም ዙሪያ ጥቅም ላይ ሊውሉ የሚችሉ እንዲሁም በዚህ ዘመን ያለውንና የወደፊቱን ትውልድ የእግዚብሔርን ቃል ለማስተማር የሚረዱ ተከታታይ የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርቶችን በማዘጋጀት ሰዎችን ማገልገልና ለአገልግሎት ብቁ ማድረግ።

**ራዕይ**

የተለያዩ የኮሙኒኬሽን አይነቶችን ስራ ላይ በማዋልና ዋና ዋና እሴቶቻችን ከሚጋሩ ግለሰቦች ጋር አብሮ በመስራት በተለየዩ የዓለም ቋንቋዎች የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርቶች ዝግጅትን ማበረታታት።

## አጠቃላይ መረጃ

### የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርቶች አገልግሎት ተግባራት ምንድናቸው?

የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርቶች አገልግሎት “ዘመነ መጽሐፍ ቅዱስ”፣ “አዲስ ሕይወት” እና “ቃራሚዎች” በሚል ርዕስ የሚታወቁ የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርቶችን በእንግሊዝኛ ያሳትማል። እንዲሁም በምድረ እንግሊዝና በሌሎች የዓለም ክፍሎች በፖስታ ቤቶች አማካኝነት በመላላክ እነኝህን ትምህርቶች የሚሰጡ የርቀት ትምህርት ቤቶችንና ሌሎች ድርጅቶችን በጉብኝት፣ በምክር፣ በኔትወርኪንግና በስልጠና ያግዛል። የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርቶች አገልግሎት በአሁኑ ጊዜ በትርጉም፣ በዲዛይን፣ በሕትመትና ትምህርቶችን በማሰራጨት ከሚሰሩና በሌሎች አገሮች ውስጥ ከሚገኙ ቡድኖች ጋር አብሮ ይሰራል።  ለሁሉም ተማሪዎች ትምህርቶቹ በነፃ እንዲዳረሱ ማድረግም ሌላው የመጽሐፍ ትምህርቶች አገልግሎት ተግባር ነው።

የመጽሐፍ ቅዱስ ጊዜ ትምህርቶች በመጀመሪያ ጥቅም ላይ የዋሉት በደቡብ አየርላንድ ከ50 ዓመታት በፊት ነበር። የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርቶች አገልግሎት በእንግሊዝኛና በሌሎች የውጭ አገር ቋንቋዎች የሚዘጋጁ የዘመነ መጽሐፍ ቅዱስ ትምህርቶችን የኤዲቶሪያል ኃላፊነት ይወስዳል።  የዘመነ መጽሐፍ ቅዱስ ትምህርቶች ሕትመት በኤ 4 ፎርማት ሆኖ በአንዳንድ አካባቢዎች የሚገኙ ተማሪዎች በአራት ሳምንት አንድ ጊዜ ትምህርቶችን ለመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት ማዕከል ለእርማት መላክ እንዲችሉ ያግዛቸዋል። ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ለቤት ለቤት ጀማ ወንጌል (የተሐድሶ ንቅናቄ) ምስጋና ይግባውና በቤልፋስት የ6 ወራት ትምህርቶች በኤ 5 ፎርማት ማዘጋጀት ተችሏል። ይህም ትምህርቶች በት/ቤቶችና በየአብያተ ክርስቲያናቱ በቀላሉ ጥቅም ላይ እንዲውሉ አስችሏል። ይህ ደግሞ ጥሩ የፖስታ አገልግሎት በሌለባቸው አካባቢዎች ውጤታማ ሆኗል።

የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርቶች አገልግሎት ኮርሶችን ልዩ የሚያደርጋቸው የቤት ለቤት ወይንም ደግሞ በቤተ ክርስቲያንና በት/ቤቶች የሚካሄዱ የቡድን ጥናቶችን ግንዛቤ ውስጥ አስገብተውና በሚገባ የታቀደ ሲለበስን ተከትለው ተማሪዎች ጥናታቸውን እድሜያቸው 20 ዓመት እስኪሆነው ድረስ እንዲቀጥሉ ስለ ሚረዷቸው ነው። ለየእድሜ ደረጃው የሚመጥኑ በአምስት ደረጃዎች የተከፋፈሉ ትምህርቶች ቀርበዋል። ቅድመ መደበኛ ትምህርት፣ ከ5-7 ዓመት፣ ከ8-10 ዓመት፣ ከ11-13 ዓመት፣ ከ14-16 ዓመት። ለእያንዳንዱ የእድሜ ክልል የሶስት ዓመት ሲለበስ ተዘጋጅቷል። (ገፅ አራትን ይመልከቱ።) እያንዳንዱ የእድሜ ክልል ባሉት ችሎታዎች መሠረት ይለያያል። የዘመነ መጽሐፍ ቅዱስ ትምህርቶች ልጆች የእግዚአብሔርን ቃል እንዲያጠኑ እድል ይፈጥርላቸዋል። ይህም የተለያዩ የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪኮችን እንዲማሩና ወንጌልን በሕይወታቸው ለመተግበር በሚያደርጉት ጥረት የሚገጥሟቸውን ተግዳሮቶች መጋፈጥ እንዲችሉ በማገዝ ነው።

የእነኝህ ትምህርቶች ኮፒዎች በእንግሊዝኛ ከመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርቶች አገልግሎት ዌብ ሳይት (www.besweb.com) ላይ ማውረድ ይቻላል። የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርቶች አገልግሎት አብረውት በአጋርነት መስራት ለሚፈልጉ ሰዎች የሚጠቅሙ ዶክሜንቶች አሉት። እነኝህ ዶክሜንቶች በመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርቶች አገልግሎት ዌብ ሳይት ላይ ይገኛሉ።

## የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርቶች አገልግሎት አድራሻዎች

**ዓለም አቀፍና የሰሜን አየርላንድ ፀሐፊ (የሁሉም ትምህርቶች አከፋፋይ)**
Mr S Balmer, 37a Belmore Street, Enniskillen, Northern Ireland BT74 6AA
ስልክ: 0286 632 2462
ኢሜይል: sam@besweb.com

**የዩናይትድ ኪንግደም ፀሐፊ**
Mr Stephen Gillham, 32 Firs Glen Road, West Moors, Ferndown, Dorset BH22 0ED
ስልክ: 01202 873500
ኢሜይል: stephen@sgilllham.co.uk

**ዌብ ሳይት**: www.besweb.com
**የኢሜይል አድራሻ**: info@besweb.com

## ለመምህራን መምሪያዎች

የዘመነ መጽሐፍ ቅዱስ ትምህርቶች በመጀመሪያ ሲዘጋጁ በፖስታ በመላላክ ለማስተማር ታስበው ነበር። ለዚህም ይረዳ ዘንድ የፖስታ መጽሐፍ ቅዱስ ት/ቤት ማዕከላት ተቋቁመው ነበር። ነገር ግን የፖስታ አገልግሎት አስተማማኝ ባልሆነባቸው እስከጭራሹንም እየቀረ በሚሄድባቸው ስፍራዎች በተለይም ደግሞ በአፍሪካና በሕንድ እንዲሁም በሌሎች የዓለማችን ክፍሎች በስፋት ጥቅም ላይ እየዋሉ ነው። በዚህ ሁኔታ ውስጥ የዘመነ መጽሐፍ ቅዱስ ትምህርቶችን ለሚጠቀሙ የማስተማሪያ መምሪያዎችም ተዘጋጅተዋል። በዚህ ጥራዝ ውስጥ የተዘጋጁት የመምህሩ መምሪያዎች ታሳቢ ያደረጉት ደረጃ 1 እና 2ን በግምት እድሜያቸው ከ5-10 ዓመት የሆኑ ልጆችን ነው።

እያንዳንዱ የመምህሩ መምሪያ ልክ ***በዘመነ መጽሐፍ ቅዱስ*** ትምህርት ውስጥ የተጠቀሱ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎችን ተከትሎ የተዘጋጀ ነው። የዘመነ መጽሐፍ ቅዱስ ትምህርቶችና መምሪያዎቻቸው በየሳምንቱ እንዲጠኑ ተደርገው ተዘጋጅተዋል። የሚያዚያ ትምህርቶች በተለይ ከፋሲካ ጋር የተገናኙ ትምህርቶች ሲሆኑ የታህሳስ ትምህርቶች ደግሞ ከጌታችን ከኢየሱስ ክርስቶስ ልደት ጋር የተገናኙ ናቸው።

በአንዳንድ ቦታዎች በኤ 4 የወረቀት መጠን የሚዘጋጀውን ሳምንታዊ ሕትመት ሲጠቀሙ በሌሎች ቦታዎች ደግሞ 24 ትምህርቶችን የያዘውንና በኤ 5 የወረቀት መጠን የተዘጋጀውን ጥራዝ ይጠቀማሉ። መምህሩ ወይንም ደግሞ የጥናቱ/የትምህርቱ መሪ በኤ 4 የወረቀት መጠን ትምህርት ያድላል። ትምህርቱም በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ወይንም ደግሞ በት/ቤት ይሞላል ወይንም ደግሞ ወደ ቤት ይወሰዳል። ከዚያም በተከታዩ ሳምንት ይመለሳል። በወሩ መጨረሻ መምህሩ ወይንም የጥናቱ/የትምህርቱ መሪ ትምህርቶችን ይሰበስብና ያርማቸዋል። ነጥብም ይሰጣቸዋል። በተቻለ መጠንም ከእርማት በኋላ ለተማሪዎች መመለስ አለበት።

የተዘጋጁት ጥራዞች ጥቅም ላይ ከዋሉ በየሳምንቱ መጨረሻ እየተሰበሰቡ ይታረማሉ። በብዙ ምክንያቶች ይህ አስቸጋሪ እንደሆነ እንረዳለን። ስለዚህም በክፍል ውስጥ ጥራዞቹ ለተማሪዎች ይከፋፈላሉ። በዚህ ጊዜ መምህሩ/መሪው ከተማሪዎች ጋር አብሮ ይሰራል። ተማሪዎችም የጓደኞቻቸውን ስራዎች ያርማሉ፣ ነጥብም ይሰጣሉ። ከጥራዞቹ በስተጀርባ ለእያንዳንዱ ነጥብ መመዝገቢያ ሰንጠረዥ እንዲሁም ተማሪው ስላሳየው እድገት አስተያየት መስጫ ቦታ አለ። እንዲሁም ከጥራዙ በስተመጨረሻ ሰርተፊኬት ተያይዟል። ይህ ሰርተፊኬት በቀላሉ ከጥራዙ ላይ ሊገነጠል የሚችል ሲሆን ተማሪው ባለፉት 6 ወራት ከመቶ ያገኛቸውን ውጤቶች ይይዛል።

## ለመምህራን የተደረገ ዝግጅት

*መምህራን በራሳቸው ዘዴ ወይንም መንገድ፣ ተነሳሽነትና ሀሳብ ላይ የተመሠረተ አንዳችም ነገር እንዲያደርጉ አንጠብቅም። ለእንደዚህ አይነት ጉዳይ ምንም ቦታ አንሰጥም። የሚከተሉት ሀሳቦች የዘመነ መጽሐፍ ቅዱስ ትምህርቶችን ለመጠቀም የሚያስፈልጉ ጠቃሚ ሀሳቦች ናቸው።*

- **ከታሪኩ ጋር በሚገባ ራስን ማስተዋወቅ** - ከመጽሐፍ ቅዱስ ታሪኮችና በተጓዳኝ አብረውት ከሚሄዱት የዘመነ መጽሐፍ ቅዱስ ትምህርቶች ጋር በተቻለ መጠን ራሳቸውን ማስተዋወቅ አለባቸው። መምህሩ የዘመነ መጽሐፍ ቅዱስ ትምህርቶችን ከማስተማሩ በፊት ራሱ አጥንቶ ቢያጠናቅቅ ተመራጭ ነው። ለእያንዳንዱ ትምህርት የተዘጋጁት መምሪያዎችም በእቅድ ወቅት ስለ ሚረዱ በጥንቃቄ ሊታዩ ይገባል።
- **ትምህርቶችን በሚገባ መረዳት** - ከእያንዳንዱ የትምህርት እቅድ በላይ *"በዚህ ክፍል የምንማራቸው የሚከተሉትን ነው።"* የሚሉ ቃላት ይገኛሉ። እነኝህም መምህሩ ገለፃውን ካጠናቀቀ በኋላና ተማሪዎችም ያንን የዘመነ መጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ከተማሩ በኋላ የሚጨብጧቸውን ሁለት አላማዎች የያዙ ናቸው። የመጀመሪያው አላማ ከታሪኩ ስለ ቀሰሙት እውቀት ነው። ሁለተኛው ደግሞ ተማሪዎች ስላገኙት እውቀት እንዲያሰላስሉና በተቻለ መጠንም ምላሽ እንዲሰጡና ከሕይወታቸው ጋር እንዲያዛምዱት ያበረታታል። እነኝህ የመማር አላማዎች በተሰጠው ትምህርት ውስጥ ያለውን ዋና ፅነሰ ሀሳብ/እውነት የያዙ ናቸው። መምህራንም ራሳቸውን እንዲሁም የመማር የማስተማር ሂደቱን ለመገምገም ሊጠቀሙባቸው ይችላሉ።
- **አስተዋውቁት/መግቢያ** - ሁሉንም ትምህርቶች የምንጀምረው ከራሳቸው ከተማሪዎች ልምምድና ካሉበት ሁኔታ በመነሳት ነው። ታሪኮችን በመግቢያው ውስጥ ለማስተዋወቅ የተለያዩ ዘዴዎችን አቅርበናል። በዚህም ልጆች በትምህርቱ ማስጀመሪያ ነጥብ ላይ በመስተጋብር የተሞላ ውይይት እንዲያካሂዱ እናስችላቸዋለን።
- **የማስተማር ጊዜ** - የታሪኩን ቁልፍ ነጥቦች አቅርበናል። መምህራን ታሪኮቹን በሚያስተምሩበት ወቅት እነኝህን ቁልፍ ነጥቦች እንደማያነሷቸው ተስፋ እናደርጋለን። ሆኖም በሚያስምሩበት ወቅት ራሳቸውን ከታሪኩ ጋር በሚገባ አስተዋውቀው ውጤታማ በሆነ መንገድ ለማስተማር ይጠቀሙባቸዋል። መምህሩ በትምህርቱ ውስጥ ያለውን ታሪክ ተማሪዎቹ በሚገባ እንዲረዱ ማድረግ አለበት። እንዲሁም ልጆቹ ታሪኩን ከተገነዘቡት በኋላ መስጠት ስላለባቸው ምላሽ አቅጣጫ ይጠቁማቸዋል። ከእያንዳንዱ ትረካ ጋር አብሮ የሚሄዱ ማብራሪያዎችንም አብረን ማቅረቡ ተገቢ ስለሆነ ይህንኑ አድርገናል። እነኝህም በኢታሊክስ (*ITALICS)* ተፅፈው ቀርበዋል።
- **የመማር ጊዜ** - ከእያንዳንዱ ታሪክ ጋር አብሮ የተያያዘ ቁልፍ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅስ አለ። አንዳንድ ጊዜም ሁለት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች ተያይዘዋል። ምክንያቱም ተጨማሪው የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅስ ተማሪዎች በቀላሉ መማር እንዲችሉ ያግዛቸዋል። ልጆች እነኝህን ቁልፍ ጥቅሶች እንዲማሩ እንዲሁም በተደጋጋሚ እንዲያስታውሱት እንደሚደረግ ተስፋ እናደርጋለን። ይህም ልጆች የቁልፍ መጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች እውቀት ግንባታ ማድረግ እንዲጀምሩ ይረዳቸዋል።
- **ማጠናቀቅ** - በት/ቤት ውስጥ ተማሪዎች ሰርቶ ማሳያ/የመለማመጃ ጥያቄዎችን ለማጠናቀቅ የሚያስፈልጋቸውን የችሎታ ልክና መምህሩ በዚህ ረገድ ለተማሪዎቹ ሊያደርግላቸው የሚችለውን የእገዛ መጠን በተመለከተ ግንዛቤ ሊኖራችሁ ይገባል። አንዳንዶች መምህሩ ታሪኩን ካነበበላቸውና ከታሪኩ ጋር በሚገባ ከተዋወቁ በኋላ ወደ ስራ ይገባሉ። ሌሎች ልጆች ደግሞ ታሪኩን ራሳቸው ማንበብ ይችላሉ። በሁለቱም መንገዶች ዋናው ሀሳብ ጥያቄዎቹን ለመስራት በተሰጠው ትዕዛዝ ላይ የልጆቹ አትኩሮት እንዲያርፍ ማድረግ ነው። የዘመነ መጽሐፍ ቅዱስ ትምህርቶችን ከት/ቤት ውጪ በሌሎች ቦታዎች የምትጠቀሙ ከሆነ ተማሪዎቻችሁን ባሉበት ቦታ በአካል ተገኝታችሁ መርዳት መቻል አለባችሁ። አለበለዚያ ተማሪዎቻችሁ ትምህርቱን እንደፈተና ወይንም ደግሞ

የግድ መጠናቀቅ እንደላበት ስራ አድርገው ሊቆጥሩት ይችላሉ። አስደሳች መሆን አለበት። ለዚህም ተማሪዎች እየሰሩ ባለበት ወቅት ማበረታታት አስፈላጊ ነው።

- **የክለሳ ጊዜ** - በተቻለ መጠን ተማሪዎች በምን ያህል መጠን ትምህርቱን አውቀውታል የሚለውን ጥያቄ ለመመለስ የሚረዱንን አጫጭር ሙከራዎችን መስጠት ወይንም አስፈላጊ መሆኑን እንመክራለን። ይህም ትምህርቱን ለመከለስና የተማሪዎችን የመማር ፍጥነት ለማገዝ ጠቀሜታው ከፍተኛ ነው።
- **ማሳየት** - በአንዳንድ ሁኔታዎች የቪዡዋል (የእይታ) ትምህርት መርጃዎች በቀላሉ ላይገኙ ቢችሉም በተቻለ መጠን ለሚታዩ ስዕሎች ወይንም ደግሞ ለሌሎች ቁሳቁሶች ትኩረት መስጠትና በተግባር ማዋል ተማሪዎች ትምህርቱን በቀላሉ መረዳት እንዲችሉ ይረዳቸዋል። በትረካ ወቅት የእይታ ትምህርት መርጃዎች ትልቅ እገዛ ያደርጋሉ። አስፈላጊ የሆኑ ስዕሎችን በተመለከተ መረጃ ከተፈለገ ከሚከተለው ዌብ ሳይት ማግኘትና ስዕሎችንም ማውረድ ይቻላል። [www.freebibleimages.org (FBI)] ሌላው የእይታ መርጃዎችን የምናገኝበት ምንጭም Eikon Bible Art [info@eikonbibleart.com] ዌብ ሳይት ነው። ሆኖም ከዚህ ዌብ ሳይት የምናገኛቸው ምንጮች በሽያጭ የሚገኙ ናቸው። የፎቶ ኮፒ ማሽን ባለበት አንዳንድ ስእሎች ሊተልቁ ቀለም ሊቀቡና በትምህርት ወቅት ጥቅም ላይ ማዋል ሊውሉ ይችላሉ።

**ቁልፍ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶችን የማስተማር ጊዜ**

1) ጥቅሱ በወረቀት ወይንም በጥቁር ሰሌዳ ላይ ሊፃፍ ይችላል። ይህም የተለያዩ ቃላትን በማጉደል የሚደረግ ነው። ይህም ሁሉም የጥቅሱ ቃላት በሙሉ እስኪነሱና ተማሪዎችም ጥቅሱን በቃላቸው መድገም እስኪችሉ ድረስ ነው።
2) ቁልፍ ጥቅሱን ለማስተዋወቅ የሚከተሉትን ማድረግ ትችላላችሁ።
   ሀ) በሁለት ቡድኖች መስራት (በገመድ የመስቀል ዘዴ) – የቁልፍ ጥቅሱ የተለያዩ ፊደላት ተቀንሰው በምትካቸው ክፍት ቦታዎች አሉ። ልጆችም የትኞቹን ቃላት ቢጠቀሙ ጥቅሱን ማሟላት እስከሚችሉ ድረስ ይሰራሉ። ይህም ከመካከላቸው አንደኛው ልጅ ጥቅሱን እስከሚለየው ድረስ ይቀጥላል።
   ለ) ጥቅሱን ቀድሞ መፈለግ። መጽሐፍ ቅዱስ በቀላሉ የሚገኝ ከሆነ ተማሪዎች ቁልፍ ጥቅሱን ይፈልጋሉ። መጀመሪያ ጥቅሱን ያገኘው ልጅ አሸናፊ ይሆናል።

**ጊዜን ማቀድ**

- **ቅደም ተከተል** ለሁሉም የማስተማሪያ መምሪያዎች ተመሳሳይ ቅደም ተከተል እንጠቀማለን። ሆኖም ይህን ቅደም ተከተል መምህራን እንደአስፈላጊነቱ ሊቀያይሩት ይችላሉ።
   1. መግቢያና ትረካ - በግምት 15 ደቂቃ
   2. ቁልፍ ጥቅሱን የማስተማር ጊዜ – ከ5 እስከ10 ደቂቃ
   3. ስርቶ ማሳያውን ማጠናቀቅ - 20 ደቂቃ
   4. መልመጃና ሌሎች ስራዎች 5-10 ደቂቃ

ይህን አባባል ሁሌም አስታውሱት።

“የነገራችሁኝን እረሳለሁ።
የምታሳዩኝን አስታውሳለሁ።
አብሬያችሁ ስሰራ በሚገባ እረዳለሁ።”

## የዘመነ መጽሐፍ ቅዱስ ትምህርቶች ሲለበስ

| | ደረጃ 0 (ቅድመ መደበኛ ትምህርት)<br>ደረጃ 1 (ከ5-7 ዓመት)<br>ደረጃ 2 (ከ8-10 ዓመት) | ደረጃ 3 (ከ11-13 ዓመት) | ደረጃ 4 (14 ዓመትና ከዚያ በላይ) |
|---|---|---|---|
| የጀማሪዎች ተከታታይ ትምህርቶች | 1. የጀማሪዎች ትምህርት - መግቢያ<br>2. ሀ1 - የሉቃስ ወንጌል<br>3. ሀ2 - የሉቃስ ወንጌል<br>4. ሀ2 - የሉቃስ ወንጌል | 1. የጀማሪዎች ትምህርት - መግቢያ<br>2. ሀ1 - የሉቃስ ወንጌል<br>3. ሀ2 - የሉቃስ ወንጌል<br>4. ሀ2 - የሉቃስ ወንጌል | 1. የጀማሪዎች ትምህርት - መግቢያ<br>2. ሀ1 - የሉቃስ ወንጌል<br>3. ሀ2 - የሉቃስ ወንጌል<br>4. ሀ2 - የሉቃስ ወንጌል |
| ሀ/ ተከታታይ ትምህርቶች | 1. ፍጥረት<br>2. ኖህ<br>3. ጴጥሮስ<br>4. ጴጥሮስ - መስቀሉ<br>5. አብርሃም<br>6. አብርሃም<br>7. ጴጥሮስ<br>8. ጴጥሮስ<br>9. ያዕቆብ<br>10. የመጀመሪያዎቹ ክርስቲያኖች<br>11. ጳውሎስ<br>12. የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ልደት ታሪክ | 1. ፍጥረት<br>2. ኖህ<br>3. ጴጥሮስ<br>4. ጴጥሮስ - መስቀሉ<br>5. ጴጥሮስ<br>6. አብርሃም<br>7. ያዕቆብ<br>8. ፀሎት<br>9. ጳውሎስ<br>10. ጳውሎስ<br>11. ጳውሎስ<br>12. የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ልደት ታሪክ | 1. ፍጥረትና ውድቀት<br>2. ዘፍጥረት የመጀመሪያዎቹ ክንዋኔዎች<br>3. ጴጥሮስ<br>4. ጴጥሮስ - መስቀሉ<br>5. ጴጥሮስ<br>6. አብርሃም<br>7. ያዕቆብ<br>8. የክርስቲያን ሕይወት<br>9. ጳውሎስ<br>10. ጳውሎስ<br>11. ጳውሎስ<br>12. የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ልደት ታሪክ |
| ለ/ ተከታታይ ትምህርቶች | 1. የክርስቶስ የቀደመው ሕይወቱ<br>2. ተአምራት<br>3. ቢታኒያ<br>4. መስቀሉ<br>5. ምሳሌዎች<br>6. ዮሴፍ<br>7. ዮሴፍ<br>8. ኢየሱስ የተገናኛቸው ሰዎች<br>9. ሙሴ<br>10. ሙሴ<br>11. ሙሴ<br>12. የጌታችን የኢየሰሰ ክርስየሰ ልደት ታሪክ | 1. ምሳሌዎች<br>2. ተአምራት<br>3. ቢታኒያ<br>4. መስቀሉ<br>5. የመጀመሪያዎቹ ክርስቲያኖች<br>6. ዮሴፍ<br>7. ዮሴፍ<br>8. የወንጌል ፀሐፊዎች<br>9. ሙሴ<br>10. ሙሴ<br>11. ሙሴ<br>12. የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ልደት ታሪክ | 1. ምሳሌዎች<br>2. ተአምራት<br>3. ቢታኒያ<br>4. መስቀሉ<br>5. የመጀመሪያዎቹ ክርስቲያኖች<br>6. ያዕቆብና ቤተሰቡ<br>7. ዮሴፍ<br>8. የሐዋርያት ስራ 2፡42 ከፊት ለፊት ያለው መንገድ<br>9. ሙሴ<br>10. ሙሴ<br>11. ሕግ<br>12. የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ልደት ታሪክ |
| ሐ/ ተከታታይ ትምህርቶች | 1. ዳንኤል<br>2. ተጨማሪ ተአምራት<br>3. ኢየሱስ የተገናኛቸው ሰዎች<br>4. የክርስቶስ ሞት<br>5. ሩትና ሳሙኤል<br>6. ዳዊት<br>7. ዳዊት<br>8. ኢያሱ<br>9. ኤልያስ<br>10. ኤልሳዕ<br>11. ዮናስ<br>12. የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ልደት ታሪክ | 1. ዳንኤል<br>2. ኢየሱስ የተገናኛቸው ሰዎች<br>3. ተጨማሪ ተአምራት<br>4. የክርስቶስ ሞት<br>5. ሩት<br>6. ሳሙኤል<br>7. ዳዊት<br>8. ኢያሱ<br>9. ኤልያስ<br>10. ኤልሳዕ<br>11. እግዚአብሔር የተጠቀማባቸው የብሉይ ኪዳን ዘመን ሰዎች<br>12. የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ልደት ታሪክ | 1. ዳንኤል<br>2. የኢየሱስ አባባሎች<br>3. የጌታ ኃይል<br>4. የክርስቶስ ሞት<br>5. ሩት<br>6. ሳሙኤል<br>7. ዳዊት<br>8. ኢያሱ<br>9. ኤልያስ<br>10. ኤልሳዕ<br>11. ተጨማሪ የብሉይ ኪዳን ባሕርያት<br>12. የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ልደት ታሪክ |

## <u>ሀ1 ታሪክ 1</u>

## እግዚአብሔር አለምን ሰራ። ይህ ታሪክ እግዚአብሔር ሰማይንና ምድርን እንዴት እንደፈጠረ ይናገራል።

| | |
|---|---|
| | **በዚህ ክፍል የምንማራቸው የሚከተሉትን ነው።**<br>• እግዚአብሔር አለምን እንደፈጠረ እንማራለን።<br>• እግዚአብሔርን ለሰራው ስለ ሁሉም ነገር ማመስገን እንዳለብን እንማራለን።<br><br>**ቁልፍ ጥቅስ:** **ዘፍጥረት 1:1**<br>**የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል : ዘፍጥረት 1: 1-19** |
| *መግቢያ* | • የቤት ስዕል አሳያቸው ወይንም ደግሞ ልጆች የራሳቸውን ቤት ስዕል እንዲሰሩ ጠይቋቸው።<br>• ሰለቤቱ ልጆችን ጥያቄ ጠይቋቸው። ገንብቶ ለማጠናቀቅ ምን ያህል ጊዜ ይፈጃል? ለግንባታ ምን ምን ያስፈልጋል?<br>• ቤት ለመገንባት ብዙ አይነት ቁሳቁሶች ያስፈልጋሉ። እግዚአብሔር ግን አለምን የፈጠረ ከምንም ነገር ተነስቶ ነው። |
| የማስተማር ጊዜ | • በመጀመሪያ እግዚአብሔር ሰማይንና ምድርን ፈጠረ። ዘፍ.1.2፤ ምድርም ባዶ ነበረች፥ አንዳችም አልነበረባትም፤ ጨለማም በጥልቁ ላይ ነበረ፤ የእግዚአብሔርም መንፈስ በውኃ ላይ ሰፍፎ ነበር። (**ዘፍጥረት 1:1-3**) - ሁልጊዜ ጨለማ ቢሆን ምን ይመስላል? (የልጆችን አይን በጨርቅ በማሰር ማስረዳት ይቻላል።)<br>• በመጀመሪያው ቀን እግዚአብሔር "ብርሃን ይሁን!" አለ። ወዲያው ብርሃን ሆነ። ብርሃኑን ቀን ብሎ ጠራው። ጨለማውን ልሊት ብሎ ጠራው። ሁል ጊዜ ጨለማ በመሆን ፈንታ ከጨለማው በኋላ ብርሃን ሆነ። (**ዘፍጥረት 1:4-5**)<br>• በሁለተኛው ቀን እግዚአብሔር በምድር ዙሪያ ሰማይና አየር ይሁን ብሎ ተናገር። ሰማይንና አየርንም ፈጠረ። ጨለማ ሆነ ሁለተኛው ቀንም ተፈፀመ። (**ዘፍጥረት 1:6-8**) - *ልጆች በረዥሙ እንዲተነፍሱ አድርጓቸው። በዙሪያችን ያለው አየር እንዴት አስፈላጊ እንደሆነ አስረዷቸው።*<br>• እስከዚህ ጊዜ ድረስ ምድር በውኃ ተሸፍና ነበር። አሁን መሬት የሚፈጠርበት ጊዜ ነው። እግዚአብሔር ተናገረ። አዲስ ምድርም ተገኘ። መሬትን የከበበው ውኃም ባሕር ሆነ። እግዚአብሔርም "ምድር በተለያዩ አይነቶች ዛፎችና ተክሎች ትሞላ።" ብሎ ተናገረ። እግዚአብሔርም የሰራውን ሁሉ ተመልክቶ "ሁሉም መልካም ነው አለ።" ይህም ሶስተኛው ቀን ነው። (**ዘፍጥረት 1:9-13**) *ልጆችን በአካባቢያቸው የሚበቅሉና የሚያውቋቸውን የአትክልት አይነቶች እንዲናገሩ ጠይቋቸው። ስለ ተለያዩ የተክሎች ቀለማት፣ ቅርፅና መጠን አውሩ። እንዲሁም ተክሎች እንዴት ውብ እንደሆኑ ንገሯቸው።*<br>• በአራተኛው ቀን እግዚአብሔር በሰማይ ላይ የሚያበሩ ብርሃናትን ፈጠረ። ፀሐይን ለቀን እንዲሁም ጨረቃና ከዋክብት ለሌሊት። እግዚአብሔርም የፈጠራቸው ብርሃናት መልካም እንደሆኑ አየ። ((**ዘፍጥረት 1:14-19**) *ፀሐይ እንዴት መልካም እንደሆነች አውሩ። በሰማይ ላይ በምታዮቸው ከዋክብት ብዛትም አድናቆታችሁን ግለፁ።*<br>• *እግዚአብሔር ምድርን ሲፈጥር ለሰው ልጆች የሚያስልጓቸውን ነገሮች አሟልቶ መሆኑን ለልጆቹ ንገሯቸው። በዚህም እግዚአብሔርን እንዲያመሰግኑ ጠይቋቸው።.*<br><br>**የዘመነ መጽሐፍ ቅዱስ ትምህርቶችን አጠናቁ ።** |
| *የመማር ጊዜ* | እንደአስፈላጊነቱ የመጽሐፍ ቅዱስ ቁልፍ ጥቅሶችን አብራሩ፣ አስተምሩ። (**ዘፍጥረት 1:1**) |
| አስታውሱት | • በመጀመሪያ ምድር ምን ትመስል ነበር?<br>• ብርሃን የተከሰተው መቼ ነበር?<br>• በሁለተኛው ቀን እግዚአብሔር ሰማያትንና _ _ _ _ _ _ _ _ _ _ _ _ ፈጠረ።<br>• በመጀመሪያ ምድር በምን ተሸፍና ነበር?<br>• በሶስተኛው ቀን እግዚአብሔር የፈጠራቸው ሁለቱ የሚያድጉ ነገሮች ምንድናቸው?<br>• ለቀን እግዚአብሔር የፈጠረው ብርሃን ምን ነበር?<br>• ለሌሊት እግዚኢብሔር የፈጠራቸው ብርሃናት ምንድናቸው?<br>• ይህን ጥቅስ አሟሉት። "በመጀመሪያ እግዚአብሔር ____________________ ፈጠረ።" |

<u>ሀ1 ታሪክ 2</u>

**እግዚአብሔር እንስሳትንና ሰዎችን ፈጠረ። ይህ ታሪክ መጀመሪያ ስለ ተፈጠረው ሰው ነው።**

| | |
|---|---|
| | **በዚህ ክፍል የምንማራቸው የሚከተሉትን ነው።**<br>• እግዚአብሔር ሰውን በአምሳሉ መፍጠሩንና ለእርሱ ሰው ማለት ልዩ ፍጥረት እንደሆነ እንማራለን።<br>• እግዚአብሔር ስለ ፈጠረን የእርሱን መንገድ መከተል እንዳለብን እንማራለን።<br>**ቁልፍ ጥቅስ :** **ዘፍጥረት** 1: 31<br>**የጥናት ክፍል :** **ዘፍጥረት** 1: 20 – 2: 3 |
| *መግቢያ* | • እናንተ የሰራችሁትና ጥቅም የማይሰጥ ነገር ይዛችሁ ኑ። ለምሳሌ ያረረ ዳቦ። ነገሮች እንደታቀደው ካልሆኑ ምን ያህል ቅር እንደሚያሰኝ አውሩ።<br>• እግዚአብሔር ብዙ ነገሮችን እንደፈጠረና በአንዳቸውም ቅሬታ እንዳልነበረው ለልጆቹ ግለፁላቸው።<br>• ወይም ልጆች ልዩ ልዩ እንስሳትን ወክለው ጨዋታ እንዲጫወቱ አድርጋቸው። ይህም በመገመት የሚደረግ ጨዋታ ሊሆን ይችላል። |
| የማስተማር ጊዜ | • በአምስተኛው ቀን እግዚአብሔር በሺ የሚቆጠሩ የተለያዩ አይነት ወፎችንና አሳዎችን ፈጠረ። እግዚአብሔርም ያ መልካም እንደሆነ አየ። (**ዘፍጥረት** 1: 20-23) *ቡድኑ የሚያውቃቸውን ጥቂት የወፎችና የአሳዎች ዝርያዎችን አስቡ።*<br>• በስድስተኛው ቀን እግዚአብሔር ሌሎች እንስሳትን በሙሉ ፈጠረ። ባለ ረጅም አንገት ቀጭኔንና ባለ ስል ጥርሶቹን አንበሳና ነብርን ሳይቀር እግዚአብሔር ፈጠራቸው። (**ዘፍጥረት** 1: 24-25)<br>• እግዚአብሔር ምንም እንኳን በርካታ መልካም ነገሮችን ቢፈጥርም አሁንም አንድ በልዩ ሁኔታ ሊፈጥረው የሚገባ ፍጥረት ነበር። *ለልጆች እፍኝ አፈር አሳዮቸውና በዚህ አፈር ምን ሊሰሩ እንደሚችሉ ጠይቋቸው።* እግዚአብሔር ከምድር አፈር ወስዶ የመጀመሪያውን ሰው አበጀበት። እስትንፋሱንም እፍ ሲልበት ያ ከአፈር ያበጀው ሰው ሕያው ሆነ። የመጀመሪያው ሰው ስም አዳም ይባላል። (**ዘፍጥረት** 1: 26-31) *እግዚአብሔር ሰውን ሲፈጥረው በአምሳሉ እንደነበር አስረዷቸው። ይህ ማለት ሰው በአንዳንድ ነገሮች እግዚአብሔርን የሚመስሉ ባሕርያት እንዲኖሩት ተደርጎ ነው የተፈጠረው። በእግዚአብሔር አምሳል ስለ ተፈጠርን ከሌሎች እንስሳት እንለያለን። እንዲሁም አዳዲስ ነገሮችን የመፍጠርና የማሰብ ችሎታ አለን። ይህ ማለትም በመልካምና በክፉ መካከል ያለውን ልዩነት እንገነዘባለን ማለት ነው። እንዲሁም የእግዚአብሔርን መንገዶች መከተል እንችላለን።*<br>• እግዚአብሔር ምድርንና በእርሷ የሚገኙትን ነገሮች በስድስት ቀናት ፈጥሮ አጠናቀቀ። የመፍጠር ስራውን ሲያጠናቀቅም አረፈ። እንዲሁም ሁሉም መልካም እንደሆነ አየ። በሰባተኛው ቀን እግዚአብሔር አረፈ በሰራውም ነገር ሁሉ ተደነቀ። (**ዘፍጥረት** 2: 1-3) *በጣም ስራ ሲበዛብን ማረፍ እንደሚገባን ከልጆቹ ጋር ተነጋገሩ።*<br>• እግዚአብሔር የሰራው አለም ፍፁም እንደሆነና እግዚአብሔርም በሰራው ፍጥረት ሁሉ ደስተኛ እንደሆነ በመንገር አጠቃሉ።<br><br>**የዘመነ መጽሐፍ ቅዱስ ትምህርቶችን አጠናቁ።** |
| *የመማር ጊዜ* | እንደአስፈላጊነቱ የመጽሐፍ ቅዱስ ቁልፍ ጥቅሶችን አብራሩ፣ አስተምሩ። (**ዘፍጥረት** 1: 31) |
| የክለሳ ጊዜ | • እግዚአብሔር በስንተኛው ቀን ወፎችንና አሳዎችን የፈጠው?<br>• ስለ እነርሱስ እግዚአብሔር ምን አለ?<br>• በስድስተኛው ቀን ከእንስሳት መፈጠር ጎን ለጎን ምን ሆነ?<br>• እግዚአብሔር ሁሉንም ነገር ከፈጠረ በኋላ ምን አለ?<br>• የመጀመሪያው ሰው ስም ማን በመባል ይታወቃል?<br>• እግዚአብሔር ሰውን ለመፍጠር የተጠቀመው ምን ነበር?<br>• እግዚአብሔር አለምን ለመፍጠር ስንት ቀናት ፈጀበት?<br>• በሰባተኛው ቀን እግዚአብሔር ምን አደረገ? |

<u>ሀ1 ታሪክ 3</u>

## የመጀመሪያዎቹ ወንድና ሴት – ይህ የአዳም ሚስት ታሪክ ነው።

<table>
<tr><td></td><td>
በዚህ ክፍል የምንማራቸው የሚከተሉትን ነው።
<ul>
<li>እግዚአብሔር አዳምን ለፍጥረት በሚያደርገው እንክብካቤ የምትረዳውን ሚስት እንደፈጠረለት እንማራለን።</li>
<li>እግዚአብሔር ሁሉንም ነገር በበላይነት እንደሚቆጣጠር እንማራለን።</li>
</ul>
ቁልፍ ጥቅስ ዘፍጥረት 2: 18 ወይንም መዝሙር 24: 1<br>
የጥናት ክፍል : ዘፍጥረት 2: 4-25
</td></tr>
<tr><td>መግቢያ</td><td>
<ul>
<li>ልጆች የአትክልት ቦታ ተሞክሮ ካላቸው በአይናቸው ያዩትን የተክሎች እድገት በተመለከተ አውሩ። ወይንም ደግሞ በአካባቢያቸው የሚታወቁ የአበባ/የፍራፍሬ/የቅጠላ ቅጠል ዝርያዎችን አምጥታችሁ አሳዩቸው። ስለ አትክልት ቦታ ምንም እውቀት ከሌላቸው ሰዎች ተክሎችን የሚያሳድጉባቸው ቦታዎች መሆናቸውን ከነገራችኋቸው በኋላ ምን እንደሚመስል ለማስረዳት ሞክሩ።</li>
<li>የኤደን ገነት በአእምራችን ከምናስበው ወይንም ደግሞ በስዕል ከምንገልፀው ከማንኛውም ነገር ይልቅ እጅግ ያማረ እንደሆነ ለልጆች ንገሯቸው።</li>
<li>ስለ ኤደን ገነት ተወያዩ። – በኤደን ገነት ብትኖሩ ደስ ይላችኋል? በዚያ ብትኖሩ እናንተን የሚያስደስታችሁ ምን ሊሆን ይችላል? አዳም በኤደን ገነት ያለሔዋን ሲኖር ብቸኝነት ይሰማው ነበር ብላችሁ ታስባላችሁ?</li>
</ul>
</td></tr>
<tr><td>የማስተማር ጊዜ</td><td>
<ul>
<li>አዳም ይኖር የነበረው እጅግ ውብ በሆነው በኤደን ገነት ውስጥ ነበር። እግዘኢብሔርም ለአዳም ምግብና ውኃን ጨምሮ የሚያስፈልገውን ነገር ሁሉ ሰጠው። እንዲሁም ይህን የአትክልት ስፍራ እንዲንከባከበው ነገረው። (ዘፍጥረት 2: 15)</li>
<li>እግዚአብሔር የፈጠራቸውን ፍጡራን ሁሉ ለአዳም አሳየው። አዳምም ለሁሉም ሕያው ፍጥረታት ስም አወጣላቸው። (ዘፍጥረት 2: 19-20)</li>
<li>እግዚአብሔር አዳም ብቻውን ይሆን ዘንድ አልፈለገም። አዳም ውብ በሆኑ እንስሳት፣ በወፎች፣ በዛፎችና በሌሎች አይነት ተክሎች ተከቧል። ሆኖም እግዚአብሔር የአዳምን ሕይወት መጋራት የምትችል ልዩ የሆነች ሴት እንደምታስፈልገው አወቀ። እግዚአብሔር በአዳም ላይ ትልቅ እንቅልፍ ጣለበት። ተኝቶ ሳለም እግዚአብሔር የመጀመሪያይቱን ሴት ከአዳም የጎን አጥንት ወስዶ አበጃት። ከዚህ በኋላ አዳም ብቻውን አይደለም። አሁን ስሟ ሔዋን የምትባል አጋርና ሚስት አገኘ። እርሷም ለአዳም በአትክልት ስፍራው እንክብካቤ አጋዥ ሆነችው። (ዘፍጥረት 2: 20-24)</li>
<li>በኤደን ገነት ውስጥ ብዙ አይነት ዛፎች ነበሩ። በአትክልት ቦታው መካከለኛ ስፍራ መልካምንና ክፉውን የሚያስታውቅ ዛፍ ነበር። እግዚአብሔር አዳምንና ሔዋንን ከሁሉም አይነት ዛፎች ፍሬ መብላት እንደሚችሉ ነገራቸው። ሆኖም መልካሙንና ክፉውን ከሚያስታውቀው ዛፍ ፍሬ እንዳይበሉ አዘዛቸው። (ዘፍጥረት 2: 16-17) በት/ቤት ወይንም ደግሞ በቤት ውስጥ ልጆች የሚያውቋቸውን ሕግጋት ጥቀሱ። እነኝህ ሕግጋት ለምን ያስፈልጉናል? (ደህንነታችን እንዲጠበቅና ደስተኞች እንድንሆን) እግዚአብሔር ለአዳምና ለሔዋን እንዲታዘዙ የሰጣቸውን ሕግ ልጆቹ እንደተረዱ አረጋግጡ።</li>
<li>እግዚአብሔር አለምንና ሕግጋትን እንደፈጠረ አብራሩላቸው። ስለዚህ ሰዎች በአለም ሲኖሩ እንዴት መኖር እንዳለባቸው መወሰን የሚችል ዋነኛ እግዚአብሔር ብቻ ነው። እኛም የእግዚአብሔርን ሕግጋት መታዘዝ አለብን።</li>
</ul>
የዘመነ መጽሐፍ ቅዱስ ትምህርቶችን አጠናቁ።
</td></tr>
<tr><td>የመማር ጊዜ</td><td>እንደአስፈላጊነቱ የመጽሐፍ ቅዱስ ቁልፍ ጥቅሶችን አብራሩ፣ አስተምሩ። - ዘፍጥረት 2: 18 ወይንም መዝሙር 24: 1</td></tr>
<tr><td>የክለሳ ጊዜ</td><td>
<ul>
<li>አዳም ይኖር የነበረው የት ነው?</li>
<li>አዳም በኤደን ገነት ውስጥ ማድረግ የነበረበት ምን ነበር?</li>
<li>እንስሳት ስማቸውን ከየት አገኙ?</li>
<li>ይህን አረፍተ ነገር አሟሉ። እግዚአብሔር አዳምን ____________________ እንዲሆን ፈለገ።</li>
<li>እግዚአብሔር የአዳምን ሚስት ለመፍጠር ምን ተጠቀመ?</li>
<li>የአዳም ሚስት ስሟ ማን ነበር?</li>
<li>በኤደን የአትክልት ስፍራ ውስጥ የነበረው ልዩ ዛፍ ስም ምን ይባል ነበር?</li>
<li>መልካምንና ክፉን ስለ ሚያስታውቀው ዛፍ እግዚአብሔር የሰጠው ትእዛዝ ምን ነበር?</li>
</ul>
</td></tr>
</table>

## ሀ1 ታሪክ 4

## እግዚአብሔር የፈጠረው አለም ተበላሸ። – ይህ ኃጢአት ወደ አለም እንዴት እንደመጣ የምናይበት ታሪክ ነው።

| | |
|---|---|
| | **በዚህ ክፍል የምንማራቸው የሚከተሉትን ነው።**<br>• አዳምና ሔዋን እግዚአብሔርን ባለመታዘዛቸው የእግዚአብሔርን ፍፁም ፍጥረት በሙሉ በኃጢአት መበከላቸውን እንማራለን።<br>• እኛም እግዚአብሔርን የማንታዘዝበት ጊዜ እንዳለ ሆኖም መፀፀትና ይቅርታን መጠየቅ እንዳለብን እንማራለን።<br>**ቁልፍ ጥቅስ :** **ሮሜ 5: 12 ወይንም ሮሜ 5: 1**<br>**የጥናት ክፍል:** **ዘፍጥረት 3: 1-24** |
| *መግቢያ* | • እጅግ በጣም የሚያምር ስዕል ካመጣችሁ በኋላ ሆን ብላችሁ በላዩ ላይ በመቸከቸከና በመቅደድ ወዘተ... አበላሹት።<br>• አሁን ውይይት አካሂዱ። - በስዕሉ ላይ ምን ተከሰተ? አሁን ምን ይመስላል?<br>• እግዚአብሔርም ፍፁም የሆነ አለም እንደፈጠረና ሆኖም ሰዎች በኃጢአት እንዳበላሹት አስረዷቸው። |
| የማስተማር ጊዜ | • አለም በመጀመሪያ ሲፈጠር ሁሉም ነገር ፍፁም ነበር። ሆኖም አንድ ቀን የእግዚአብሔር ጠላት የሆነው ሰይጣን እባብን ተመስሎ ወደ ኤደን ገነት መጣ። እባቡም ሔዋንን መልካምንና ክፉውን ከሚያስታውቀው ዛፍ ፍሬ ቢበሉ ልክ እንደእግዚአብሔር ብልህ እንደሚሆኑ ነገራት።. (**ዘፍጥረት 3: 1-5**)<br>• ሔዋን የእግዚአብሔርን ጠላት ድምፅ አደመጠች። ከዚያም የእግዚአብሔርን ትዕዛዝ ተላለፈች። መልካምንና ክፉውን ከሚያስታውቀው ዛፍ ጥቂት ፍሬዎችን ወሰደች። ለአዳምም ሰጠችው። ሁለቱም በሉ።. (**ዘፍጥረት 3: 6**)<br>• በዚያን ምሽት እግዚአብሔር አዳምንና ሔዋንን ሊያነጋግራቸው ፈለገ። የእግዚአብሔርን ትዕዛዝ እንደተላለፉ ስለ ተረዱ ተደበቁ። (**ዘፍጥረት 3: 7-8**) *የአንድን ሰው ትእዛዝ አምቢ ብላችሁ የተላላፋችሁበትን ጊዜ ታስታውሳላችሁ? ያለመታዘዛችሁ ያስከተለው ውጤት ነበር? አዳምና ሔዋን ከእግዚአብሔር መደበቅ እንደማይችሉ አስረዷቸው። እኛም እንዲሁ መሸሸግ እንደማንችል አስረዷቸው።*<br>• እግዚአብሔር “ወዴት ነህ?” ብሎ ተጣራ። ትዕዛዙን እንደተላለፉ ያውቅ ነበር። ሆኖም አሁንም ይወዳቸው ነበር። ስለ መተላለፋቸው ግን መቀጣት ነበረባቸው። እግዚአብሔር አዳምንና ሔዋንን ከኤደን ገነት አስወጣቸው። ኃጢአታቸው የእግዚአብሔርን ፍጥረት በሙሉ በከሏል። ከእግዚአብሔር ጋር ያላቸውንም የወዳጅነት ግንኙነት አፍርሶታል። በአዳምና በሔዋን ኃጢአት ምክንያት እሾህና አሜኬላ መብቀል ጀመሩ። እንስሳትና ሰዎች መታመም ጀመሩ። ይባስ ብሎም ሞት ወደ አለም ገባ። (**ዘፍጥረት 3: 9-24**)<br>• *እኛም የእግዚአብሔርን ትዕዛዛት ስንተላለፍ እግዚአብሔር ያዝንብናል። ልጆች እግዚአብሔርን ሊያሳዝኑባቸው የሚችሉ አንዳንድ ነገሮችን አብራችሁ ሆናችሁ አስቡ። እንዲህም ሆኖ እግዚአብሔር ይወደናል። የእግዚአብሔር ልጅ ኢየሱስ በመስቀል ላይ በመሞት የኃጢአት ይቅርታ እንድናገኝና የእግዚአብሔር ወዳጆች እንድንሆን አድርጎናል። ይህም በእርሱ ስናምን የሚሆን ነገር ነው።*<br><br>**የዘመነ መጽሐፍ ቅዱስ ትምህርቶችን አጠናቁ።** |
| *የመማር ጊዜ* | እንደአስፈላጊነቱ የመጽሐፍ ቅዱስ ቁልፍ ጥቅሶችን አብራሩ፣ አስተምሩ። - **ሮሜ 5: 12 ወይንም ሮሜ 5: 1** |
| የክለሳ ጊዜ | • ሔዋን ፍሬውን እንድትወስድና እንድትበላ የፈተናት ማን ነበር?<br>• እንዴት ነው ፍሬውን እንድትበላ ሰይጣን ሔዋንን ያሳመናት?<br>• ሔዋን ፍሬውን ለማን ሰጠች?<br>• እግዚአብሔር አዳምንና ሔዋንን ሲጠራቸው ምን አደረጉ?<br>• እግዚአብሔር አዳምና ሔዋን ባደረጉት ነገር ምን ተሰማው?<br>• በአዳምና በሔዋን ላይ የደረሰባቸው ነገር ምን ነበር?<br>• ትክክል ያልሆኑ ነገሮችን ስናደርግ እግዚአብሔር ምን ይሰማዋል?<br>• ለምናደርጋቸው ትክክል ያልሆኑ ነገሮች ከእግዚአብሔር ዘንድ ይቅርታ ማግኘት የምንችለው እንዴት ነው? |

## ሀ2 ታሪክ 1
## ኖህ እግዚአብሔርን ታዘዘ። – ይህ የኖህ የመርከብ ግንባታ ታሪክ ነው።

| | |
|---|---|
| | **በዚህ ክፍል የምንማራቸው የሚከተሉትን ነው።**<br>• ኖህና ቤተሰቡ እንዲሁም እንስሳቱ በመርከቡ ውስጥ በመሆናቸው ከጥፋት ዳኑ።<br>• እግዚአብሔርም እኛን ለማዳን መንገድ አዘጋጀ። ስለዚህ ልክ ኖህ እንዳመነው እኛም ልናምነው እንችላለን።<br><br>**ቁልፍ ጥቅስ :** **የሐዋርያት ሥራ 16: 31**<br>**የጥናት ክፍል:** **ዘፍጥረት 6: 5-22** |
| መግቢያ | • ልጆቹ በጣም የሚወዷቸውን እንስሳት ስም እንዲነግሯችሁ ጠይቋቸው።<br>• እነኝህ የሚወዷቸው እንስሳት በሙሉ በአንድ ላይ ቢሆኑ ምን ሊፈጠር እንደሚችል ጠይቋቸው! እነርሱንስ በሙሉ በአንድ ላይ ሊይዝ የሚችል ቦታ ምን አይነት እንደሆነ ጠይቋቸው? ድምፃቸውስ በአንድ ላይ ምን ይመስላል? ጠረናቸውስ ምን ሊመስል ይችላል?<br>• በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ጥቂት ሰዎችና እጅግ በጣም ብዙ እንስሳት በአንድ ትልቅ መርከብ ውስጥ በአንድ ላይ ስለ ነበሩበት ጊዜ እንደሚማሩ ለልጆች ንገሯቸው። |
| የማስተማር ጊዜ | • እግዚአብሔር በመጀመሪያ ዓለምን ሲፈጥር ውብና መልካም አድርጎ ነበር። ከረዥም ወቅት በፊት አዳምና ሔዋን የእግዚአብሔርን ትዕዛዝ ተላለፉ። ልጆቻቸውም በእግዚአብሔር ፊት ራስ ወዳዶችና ክፉዎች ሆኑ። እግዚአብሔርም ሰዎችን ስለ ፈጠረ አዘነ። (**ዘፍጥረት 6: 5-6**)<br>• ዓለም በሙሉ በክፋት ተሞላ። ነገር ግን እግዚአብሔር ደስ የሚሰኝበት አንድ ሰው ብቻ ተገኘ! የዚህ ሰው ስም ኖህ ይባል ነበር። ይህ ሰው፣ ሚስቱ፣ እንዲሁም ሶስት ወንዶች ልጆቹና ሚስቶቹ እግዚአብሔር የሚሻውን አንድ ነገር ለመስራት ሞከሩ። በአካባቢያቸው የነበሩ ሌሎች ቤተሰቦች ግን ራሳቸውን ከማስደሰት ውጪ ስለ እግዚአብሔር ፈፅመው ረስተው ነበር። (**ዘፍጥረት 6: 8-10**)<br>• እግዚአብሔርም ዓለም ፈፅሞ መበላሸቷን ስላየ ሊቀጣት ወሰነ። እግዚአብሔርም ኖህ ትልቅ መርከብ እንዲገነባ ፈለገ። ልክ የመርከብ ግንባታው ሲጠናቀቅ ትልቅ ጎርፍ በምድር ላይ ለመላክ ወሰነ። ሕያው ነፍስ ያለው ሁሉ ይሞታል። ነገር ግን ኖህና ቤተሰቡ በመርከቡ ውስጥ ስለሆኑ ከጎርፉ ጥፋት ይድናሉ። (**ዘፍጥረት 6: 13-18**)<br>• ኖህ ሁሉንም ልክ እግዚአብሔር እንደተናገረው አደረገ። ምናልባትም ይህን ትልቅ መርከብ ለመገንባት እስከ አንድ መቶ አመታት የሚደርስ ጊዜ ፈጅቶበት ሊሆን ይችላል። *ስለ መርከቡ መጠን አውሩ። ምናልባት የአንድ የእግር ኳስ ሜዳ ስፋት ያለውና ሶስት ፎቆች ያሉት ሊሆን እንደሚችል ንገሯቸው።* በመጨረሻም ከብዙ አድካሚ ስራ በኋላ የመርከቡ ስራ ተጠናቀቀ። (**ዘፍጥረት 6: 22**)<br>• እግዚአብሔርም ኖህን ከሁሉም የእንስሳትና የወፎች ዝርያዎች ወደ መርከቡ ውስጥ እንዲያስገባ ነገረው። በመግቢያው ላይ ልጆቹ የነገሯችሁን የጥቂት እንስሳት ስም አሁን አስታውሷቸው። እነኝህ እንስሳትም ከኖህና ከቤተሰቡ ጋር በአንድነት በመርከቡ ውስጥ እንዲሆኑና ከጥፋት እንዲድኑ ተደረገ። *ወደ መርከቡ ውስጥ የገቡትን ስምንቱን የኖህ ቤተሰብ አባላት ቁጠሩ።* ሁሉም በመርከቡ ውስጥ እንደገቡ እግዚአብሔር የመርከቡን በር ዘጋው። እነርሱን ለማዳን ያወጣውን እቅድ ፈፀመ። (**ዘፍጥረት 7: 13-16**)<br>• *እኛም ብዙ ትክክል ያልሆኑ ነገሮችን እንዳደረግን ንገሯቸው። እኛም በኃጢአታችን ምክንያት ከሚደርስብን ቅጣት መዳን እንዳለብን አስረዷቸው። እግዚአብሔር ለእኛም የምንድንበትን መንገድ አዘጋጅቶልናል። ይህም በልጁ በኢየሱስ ክርስቶስ በማመን ነው። ኢየሱስ ክርስቶስ ልክ እንደመርከቡ ለእኛ ያዘጋጀው የደህንነት መንገድ ነው።*<br>**የዘመነ መጽሐፍ ቅዱስ ትምህርቶችን አጠናቁ።** |
| የመማር ጊዜ | እንደአስፈላጊነቱ የመጽሐፍ ቅዱስ ቁልፍ ጥቅሶችን አብራሩ፣ አስተምሩ። - **የሐዋርያት ስራ 16: 31** |
| የክለሳ ጊዜ | • በዓለም ውስጥ የነበረው ችግር ምን ነበር?<br>• እግዚአብሔር ምን ለማድረግ ወሰነ?<br>• እግዚአብሔርን ያስደሰተው ማን ነበር?<br>• እግዚአብሔር ኖህን ምን እንዲያደርግ አዘዘው?<br>• ወደ መርከቡ የገባው ማን ነበሩ?<br>• የመርከቡን በር የዘጋው ማን ነበር?<br>• በመርከቡ ውስጥ የነበሩ ሰዎች እንዲድኑ የተፈለገው ለምንድነው?<br>• እኛስ ከኃጢአት ቅጣት መዳን የምንችለው እንዴት ነው? |

## <u>ሀ2 ታሪክ 2</u>

## በመርከቡ ውስጥ መዳን – ይህ ታሪክ የጥፋት ውኃ አጀማመር ታሪክ ነው።

| | |
|---|---|
| | **በዚህ ክፍል የምንማራቸው የሚከተሉትን ነው።**<br>• ኖህና ቤተሰቡ እግዚአብሔርን ስለ ታዘዙና ስላመኑት መዳናቸውን እንማራለን።<br>• እኛም እግዚአብሔርን ከታመንነው ሊያድነን ቃል እንደገባልን እንማራለን።<br><br>**ቁልፍ ጥቅስ** **ምሳሌ 29: 25**<br>**የጥናት ክፍል:** **ዘፍጥረት 7: 1-16** |
| *መግቢያ* | • ልጆች ስለ ሰሩት ወይንም ስለ ገነቡት አንድ ነገር ጠይቋቸው። ያን ነገር ለመስራት ምን ተጠቀሙ? ከባድ ነበር? የረዳቸው ሰው ነበር?<br>• ያለፈውን ታሪክ መለስ ብላችሁ እዩት። ኖህ መርከቡን ለመስራት ምን ተጠቀመ? መርከቡን መስራት አስቸጋሪ ነበር ትላላችሁ? መርከቡን ለምን ሰራው?<br>• ምንም እንኳን ስራው ከባድ ቢሆንም እግዚአብሔር ስላዘዘው ብቻ ኖህ መርከቡን እንደሰራ በአትኩሮት ንገሯቸው። ሙሉ በሙሉ የእግዚአብሔርን መመሪያ ተከትሎ ተግባራዊ አድርጓል። |
| የማስተማር ጊዜ | • ኖህና ቤተሰቡ በመርከቡ ውስጥ ያለስጋት ተቀምጠው ነበር። (**ዘፍጥረት 7: 6-7**)<br>• መርከብ ውስጥ ከገቡ ከሰባት ቀን በኋላ መዝነብ ጀመረ። በየቀኑ ያለማቋረጥ መዝነቡን ቀጠለ! አበባውና ሳሩ ሁሉ በውኃ ተሸፈነ። ወንዞችና ባህሮች ሁሉ ወደ ትልቅ ኅርፍነት ተለወጡ። (**ዘፍጥረት 7: 17-20**) *አሁን በኖህ ላይ ሲስቁና ሲያላግጡ ለነበሩ ሰዎች የሚድኑበት እድልና ጊዜ እንዳለፈባቸውና ከመርከቡ ውጪ እንደነበሩ አስረዷቸው።*<br>• የውኃው መጠን እየጨመረ መሄዱን ቀጠለ። ቤቶችን፣ ዛፎችንና እንደውም ትልልቅ ተራራዎችን ሳይቀር ሸፈናቸው። (**ዘፍጥረት 7: 20-21**) *ኖህና ቤተሰቡ በመርከቡ ውስጥ ሆነው ሊሰማቸው የሚችለውን ነገር አስቡ። ኖህ እግዚአብሔርን ሳይታዘዝ ቢቀር ምን ይሆን ነበር?*<br>• በመርከቡ ውስጥ የነበሩት ኖህና ቤተሰቡ እንዲሁም እንስሳቱ ሁሉ ከጥፋት ዳኑ። ይህም ኖህ እግዚአብሔርን ስለ ታዘዘና ስላመነ ነበር። እግዚአብሔርም ጠበቀው። (**ዘፍጥረት 7: 23**)<br>• *እኛም እግዚአብሔርን እንድናምነውና እንድንታዘዘው እንደሚፈልግ ለልጆቹ አስረዷቸው። ብንታዘዘውና ብናምናው እግዚአብሔርም እኛንም ሊያድነን ቃል ገብቶልናል።*<br><br>**የዘመነ መጽሐፍ ቅዱስ ትምህርቶችን አጠናቁ።** |
| የመማር ጊዜ | እንደአስፈላጊነቱ የመጽሐፍ ቅዱስ ቁልፍ ጥቅሶችን አብራሩ፣ አስተምሩ። - **ምሳሌ 29: 25** |
| የክለሳ ጊዜ | • ኖህ እግዚአብሔርን ማመኑን ያሳየው እንዴት ነበር?<br>• ከኖህ ጋር ወደ መርከቡ የገቡት እነማን ነበሩ?<br>• ዝናብ መዝነብ ከመጀመሩ በፊት በመርከቡ ውስጥ ለምን ያህል ጊዜ ተቀመጡ?<br>• የውኃዎቹ ከፍታ ምን ያህል ነበር?<br>• ማን ዳነ?<br>• ኖህ ለምን ዳነ?<br>• ብናምነው እኛን የሚያድነን ማነው? |

<u>ሀ2 ታሪክ 3</u>

## አዲስ ጅማሬ – ይህ ታሪክ የጥፋት ውኃ ካበቃ በኋላ ስላለው ጊዜ ይተርክልናል።

| | |
|---|---|
| | **በዚህ ክፍል የምንማራቸው የሚከተሉትን ነው።**<br>• እግዚአብሔር ለኖህና ለቤተሰቡ አዲስና ንፁሕ የመኖሪያ አለምን ሰጣቸው።<br>• ከእግዚአብሔር ይቅርታን ብንጠይቅ ሕይወታችንን ንፁሕና አዲስ ሊያደርገው እንደሚችል።<br><br>**ቁልፍ ጥቅስ** **2 ቆሮንቶስ 5: 17**<br>**የጥናት ክፍል:** **ዘፍጥረት 8: 1-19** |
| *መግቢያ* | • ኖህና ቤተሰቡ በመርከቡ ውስጥ ለረዥም ጊዜ እንደቆዩ ለልጆቹ ንገሯቸው።<br>• በመርከቡ ውስጥ መሆን ምን ሊመስል እንደሚችል እንዲያስቡ ፍቀዱላቸው። እንደው ሙሉ ቀን ምን ስታደርጉ ትውሉ ነበር? ምንስ ይሰማችሁ ነበር? |
| የማስተማር ጊዜ | • ከ40 ቀናት በኋላ ዝናቡ ቆመ። ሆኖም አሁንም ተራሮች በውኖች ተሸፍነው ነበር። (**ዘፍጥረት 8: 1-4**)<br>• አንድ ቀን ኖህ መሬቱ ተገልጦ እንደሆነ ለማረጋገጥ ከመርከቡ ውስጥ ቁራን ላከ። ቁራ ግን ተመልሶ አልመጣም። ጥቂት ቆይቶም እርግብን ላከ። እርግቢቱም ተመልሳ መጣች። ከሳምንት በኋላ እርግቢቱን መልሶ ላካት። በዚህን ጊዜ እርግቢቱ በአፏ የወይራ ቅጠል ይዛ ተመለሰች። በመርከቡ ውስጥ የነበሩት ሁሉ ደስ አላቸው። *ይህ ማለት የውኖቹ ከፍታ ከዛፎቹ በታች መሆኑን እንደሚያሳይ ለልጆቹ ንገሯቸው።* (**ዘፍጥረት 8: 6-11**)<br>• ከሰባት ቀናት በኋላ ኖህ እንደገና እርግብን ላካት። በዚህ ጊዜ ግን እርግቢቱ ተመልሳ አልመጣችም። ኖህም ከዚህ የተረዳው ውኃው በጣም እየጎደለ መምጣቱንና እርግቢቱም የምታርፍበትን ጎጆ ማግኘቷን ነበር። በመጨረሻም የኖህ መርከብ አራራት በሚባለው ተራራ ላይ አረፈ። (**ዘፍጥረት 8: 12**)<br>• መሬቱ ሲደርቅም እግዚአብሔር ኖህን ከእንስሳቱ ጋር ከመርከቡ ውስጥ እንዲወጣ አዘዘው። ይህ በዚያ ለነበሩ ሁሉ እንዴት ያለ መልካም ዜና ነበር! በመርከቡ ውስጥ ለረጅም ጊዜ ተዘግቶባቸው ነበርና! *ኖህና ቤተሰቡ ከመርከቡ ውስጥ ሲወጡ ምን ስሜት የተሰማቸው ይመስላችኋል? አዲሱ አለምስ ምን ሊመስል እንደሚችል ከልጆቹ ጋር አብራችሁ አሰሳ አድርጉ።* (**ዘፍጥረት 8: 15-19**)<br>• *እኛም በኖህ ዘመን ከነበሩት ሰዎች ልንለይ እንደማንችል አስረዷቸው። በሕይወታችን ያሉ መጥፎ ነገሮችን እግዚአብሔር ሊያስወግዳቸውና ንፁሕ ልብን ሊሰጠን እንደሚችል ንገሯቸው። እግዚአብሔርን ይቅር እንዲለን መጠየቅና በመስቀል ላይ የእኛን ኃጢአት ለማስወገድ ሲል በሞተው በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ማመን እንደሚገባን ንገሯቸው።*<br>**የዘመነ መጽሐፍ ቅዱስ ትምህርቶችን አጠናቁ።** |
| *የመማር ጊዜ* | *እንደአስፈላጊነቱ የመጽሐፍ ቅዱስ ቁልፍ ጥቅሶችን አብራሩ፣ አስተምሩ።* - **2 ቆሮንቶስ 5: 17** *ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ የውስጥ ማንነታችን መለወጥ እንደሚችል እናስረዳቸው።* |
| የክለሳ ጊዜ | • ኖህ መጀመሪያ ከመርከቡ ወደ ውጭ የላከው የትኛውን ወፍ ነበር?<br>• በሁለተኛው ጊዜ እርግቢቱ በአፏ ይዛ የመጣችው ምን ነበር?<br>• መርከቡ ያረፈው የት ነበር?<br>• ኖህን ከመርከቡ ውስጥ እንዲወጣ የነገረው ማን ነበር?<br>• ከጥፋት ውኃ የዳነው ማን ነበር?<br>• ሰለእኛ ኃጢአት የተቀጣው ማን ነበር?<br>• ልባችን እንዲነፃ ምን ልናደርግ ይገባናል?<br>• የጎደሉትን ቃላት ሙሉ። "ስለዚህ ማንም በክርስቶስ ቢሆን _ _ _ _ _ _ _ _ _ _ _ _ _ _ _ _ _ _ _ _ _ _ ነው።" |

## ሀ2 ታሪክ 4
## የእግዚአብሔር ቃል ኪዳን – ይህ ታሪክ እግዚአብሔርን ስለ ማመስገን የምንማርበት ታሪክ ነው።

**በዚህ ክፍል የምንማራቸው የሚከተሉትን ነው።**

- እግዚአብሔር ሁልጊዜ ቃል ኪዳኑን እንደሚጠብቅ እንማራለን።
- እግዚአብሔር ኖህንና ቤተሰቡን እንደጠበቃቸው እኛም ብንታመንበትና ብንከተለው ፈፅሞ ላይተወን ቃል እንደገባልን እንማራለን።

**ቁልፍ ጥቅስ** **ዘኍልቅ** 10: 29 **ወይንም ዕብራውያን** 13: 5
**የጥናት ክፍል:** **ዘፍጥረት** 8: 20-22 **እና** 9: 7-17

### *መግቢያ*

- ለእናንተ ከዚህ በፊት ሰው የገባላችሁን ቃል ኪዳን በማስታወስ ለልጆቹ ንገሯቸው።
- እንዲሁ ልጆቹም ከዚህ ቀደም በሰው የተገባላቸውን ቃል ኪዳን እርስ በርስ እንዲጋሩ አድርጓቸው።
- አንድ ሰው የገባላቸውን ቃል ኪዳን ሳይፈፅምላቸው ቀርቶ እንደሆነ ልጆቹን ጠይቋቸው።
- መጽሐፍ ቅዱስ በእግዚአብሔር ቃል ኪዳን የተሞላ መሆኑንና እግዚአብሔርም ቃልኪዳኑን ሳይፈፅም የቀረበት አንድም ጊዜ አለመኖሩን ለልጆች ንገሯቸው።
- እግዚብሔርን ለመከተልና በእርሱ ለመታመን ከመረጥን በፍፁም እንደማይተወን ቃል እንደገባልን ለልጆች ንገሯቸው።

### የማስተማር ጊዜ

- ኖህ ከቤተሰቡ ጋር አብሮ ዳነ! በመርከቡ ውስጥ ለረጅም ጊዜ ቆዩ። አሁን ግን እግዚአብሔር ለኖህ እርሱ ቤተሰቡና አብረውት ያሉ እንስሳት ሁሉ መርከቡን ለቀው መውጣት እንደሚችሉ ነገረው። (**ዘፍጥረት** 8: 15-19)
- ኖህ መጀመሪያ ማድረግ የፈለገው እግዚአብሔር የጥፋት ውኃ በነበረበት ወቅት ሁሉ እርሱንና ቤተሰቡን ስላዳናቸው "አመሰግንሃለሁ" ማለት ነበር! ይህንን ያደረገውም የተወሰኑ ትልልቅ ድንጋዮችን በመሰብሰብና ደራርቦ መሰዊያን በማዘጋጀት ነበር። ኖህ በነበረበት ዘመን ሰዎች መሰዊያ ሰርተው መስዋእትን በማቅረብ እግዚአብሔር ስላደረገላቸው ነገር ማመስገን የተለመደ ነበር። (**ዘፍጥረት** 8: 20-21) *በየትኛቹ ጉዳዮቻችን ምክንያት እግዚአብሔርን ልናመሰግን እንችላለን? (በትልቅ ወረቀት ወይንም በጥቁር ሰሌዳው ላይ እግዚአብሔርን ልናመሰግንባቸው የሚገቡ ነገሮችን ዝርዝር መፃፍ እንችላለን።)*
- እግዚአብሔር ኖህና ቤተሰቡ ሊያመሰግኑት ስለ ፈለጉ ደስ ተሰኘ። ከዚያም የሚገርም ቃል ኪዳን ከእነርሱ ጋር አደረገ። "ምድርን በሞላ ከአሁን በኋላ በጥፋት ውኃ አላጥለቀልቃትም።" (**ዘፍጥረት** 8: 21-22)
- በመቀጠልም እግዚአብሔር የቃል ኪዳኑ መታሰቢያ የሆነ ነገር አሳያቸው። ይህም ቀስተ ደመና ነበር። ኖህና ቤተሰቡ ቀስተ ደመናውን ባዩ ቁጥር የእግዚአብሔርን ቃል ኪዳን ያሳስባቸው ነበር። (**ዘፍጥረት** 9: 12-13) *ስለ ቀስተ ደመናና ስለ አስገራሚ ቀለማቱ አውሩ። ከአሁን በኋላ ቀስተ ደመናን ሲያዩ የእግዚአብሔርን ቃል ኪዳኖች እንዲያስታውሱ አበረታቷቸው።*
- *እግዚአብሔር ለኖህ የገባውን ቃል ኪዳን ፈፀመ? እኛም እግዚአብሔርን ስንታመንበት ቃል ኪዳኑን እንደሚጠብቅ ልጆች እንዲረዱ አድርጓቸው። (ሁለተኛውን ቁልፍ ጥቅስ ተመልከቱ።)*

**የዘመነ መጽሐፍ ቅዱስ ትምህርቶችን አጠናቁ።**

### *የመማር ጊዜ*

እንደአስፈላጊነቱ የመጽሐፍ ቅዱስ ቁልፍ ጥቅሶችን አብራሩ፣ አስተምሩ። - **ዘኍልቅ** 10: 29 **ወይንም ዕብራውያን** 13: 5

### የክለሳ ጊዜ

- ከዚህ በፊት ከነበረው የኖህ ታሪክ የክለሳ ጊዜ ውስጥ ጥያቄዎች መርጣችሁ ልጆቹ ምን ያህሉን ማስታወስ እንደቻሉ ለማረጋገጥ ጠይቋቸው።
- ልጆች የኖህን ታሪክ ሲያጠኑ አብራችሁ ያያችኋቸውን ቁልፍ ጥቅሶች መልሳችሁ ከልሷቸው።
- ልጆች ከኖህ ታሪክ ደስ የተሰኙበትን ክፍል መርጠው ስእል መሳል ይችላሉ። ወይንም ደግሞ ስለ ተማሩት አንድ ነገር አረፍተ ነገር መፃፍ ይችላሉ።
- ልጆች በቡድን ተከፋፍለው ወይንም የክፍሉ ተማሪዎች በሙሉ በአንድነት ሆነው በመርከብ ውስጥ የነበሩ እንስሳትን ኮላዥ (collage) መስራት ይችላሉ። በዚህ ልጥፍ ስዕል ላይም ቀስተ ደመናን መጨመር ይችላሉ።

## <u>*ሀ3 ታሪክ 1*</u>

## ኢየሱስ ጴጥሮስን ለአገልግሎት ጠራው። ይህ ታሪክ ኢየሱስን ስለ መከተል ነው።

**በዚህ ክፍል የምንማራቸው የሚከተሉትን ነው።**

- ኢየሱስ በአገልግሎቱ የሚያግዙትን እንዲሁም ለወደፊትም አብረው ማገልገል የሚችሉ አገልጋዮችን እንደሚፈልግ እንማራለን።።
- ከኢየሱስ ጋር አብሮ ሰራተኞች ለመሆን ኢየሱስን መከተልና መታዘዝ እንዳለብን እንማራለን።

**ቁልፍ ጥቅስ** **ማቴዎስ** 4: 19

**የጥናት ክፍል:** **ማቴዎስ** 4: 18 - 22

### *መግቢያ*

- ስለ ጓደኞች አውሩ። ጓደኞቻቸውን ለመጀመሪያ ጊዜ የተገናኙት መቼ ነበር? ለምንድነው መልካም ጓደኞች ሊኖሩን የሚገባው? መልካም ጓደኞች ሊሆኑ የሚችሉ ምን አይነት ሰዎች ናቸው? (የዚህ ጥያቄ መልሶች ደግ፣ አጋዥ፣ አስተማማኝ... የመሳሰሉ ሊሆኑ ይችላሉ።)
- ጌታ ኢየሱስም መልካም ጓደኞች እንደነበሩትና ስለ አንዳንድ ጓደኞቹም ዛሬ እንደምንማር አስረዷቸው።
- ድርጊቱ የተፈፀመበትን አካባቢ ቅኝት ማካሄድ – በተራሮች የተከበበና ገሊላ በመባል የሚጠራው ትልቅ ባሕር ነበር። አሳ አጥማጆች በዚህ ባሕር አሳ በማጥመድ ስራ ይሰማሩ ነበር። ይህን እንዴት ያደርጉ እንደነበር አብራሩ። (በጀልባ፣ በመረብ ወዘተ...) አድካሚ ስራ ነበር!

### የማስተማር ጊዜ

- ኢየሱስ ጴጥሮስንና ወንድሙን እንድርያስን ጠራቸው። (**ማቴዎስ** 4: 18 – 19) ጴጥሮስና ዮሐንስ ከኢየሱስ ጋር ከዚህ በፊት ተገናኝተዋል። ስለዚህም ኢየሱስ እንዴት አስፈላጊ ሰው እንደሆነ ተገንዘበዋል። ኢየሱስ አሁን አሳ ማጥመዳቸውን ትተው እንዲከተሉትና አብረውት አገልጋዮች እንዲሆኑ ፈለገ! *ኢየሱስ ይህን ፍላጎቱን ያሳየባቸውን ትክክለኛ ቃላት ተጠቅማችሁ አዲሱ ስራቸው ሰዎችን ወደ ኢየሱስ ማምጣትና ኢየሱስን እንዲተዋወቁት ማድረግ እንደሆነ አስረዷቸው። ኢየሱስ እንዲሰሩ የፈቀደላቸው እንዴት አስደናቂ ስራ ነው!*
- የጴጥሮስና የእንድርያስ ምላሽ። (**ማቴዎስ** 4: 20) ይህ ትክክለኛ ምርጫ እንደሆነ ለመወሰን ጊዜ አልፈጀባቸውም። ከኢየሱስ ጋር ወዲያውኑ አብረው በመሄድ ፈቃደኝነታቸውን ገለፁ። *ልጆች ወዲያውኑ የሚታዘዙባቸውን የሕይወታቸውን ገጠመኞች በማስታወስ ከዚህ ከጴጥሮስና ከእንድርያስ መታዘዝ ጋር እንዲያወዳድሩት አድርጓቸው። ጴጥሮስና እንድርያስ በዚህ ጥሪና ጥሪውን በመታዘዝ በመቀበላቸው የሚሰማቸውን ስሜት ዳሰሳ አድርጉ። (አድናቆት፣ ደስታ፣ ልዩ የመሆን ስሜት ወዘተ... ምክንያቱም የታዘዙት ጥሪ የመጣው ከኢየሱስ ከራሱ ስለ ነበር።) ለደረጃ 2 ልጆች አሁን እነጴጥሮስ የኢየሱስ ደቀመዛሙርት መሆናቸውን ንገሯቸው። ይህ ማለትም ኢየሱስን በሚሄድበት ቦታ ሁሉ ይከተሉታል እንዲሁም ከእርሱ መማርና መታዘዝ ይችላሉ ማለት ነው።*
- ኢየሱስ ያዕቆብንና ዮሐንስን ለአገልግሎት ጠራቸው። (**ማቴዎስ** 4:21 - 22) በዚያ ቀን አረፋፈዱ ላይ ሁለት ሌሎች አሳ አጥማጆችንም ጠራቸው። እነርሱም ተከተሉት። (ደረጃ 2)
- *ኢየሱስ ሁላችንም እንድንከተለው ይፈልጋል። ተከታዮቹ ከሆንን በስራው ውስጥ ተሳታፊዎች አድርጎ ይጠቀምብናል። በዚህ የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ ውስጥ እንደተገለፀው የኢየሱስን ቃል መታዘዝ አለብን። የተፃፈልንን የኢየሱስን ቃል የምናገኘው የት ነው? (የመጽሐፍ ቅዱስን አስፈላጊነት አስረዷቸው።)*

**የዘመነ መጽሐፍ ቅዱስ ትምህርቶችን አጠናቁ።**

### የመማር ጊዜ

ቁልፍ ጥቅሱን ስታስተምሯቸው ልጆች "የሰው አጥማጅ" የሚለውን ሀሳብ መረዳታቸውን አረጋግጡ። **ማቴዎስ** 4: 19

### የክለሳ ጊዜ

- በአጠቃላይ ስንት አሳ አጥማጆችን ነው ኢየሱስ የጠራው?
- የሚሰሩት የት ነበር?
- የእንድርያስ ወንድም ማን ነበር?
- ኢየሱስ ቃል የገባላቸው ምን እንደሚሆኑ ነው?
- ጴጥሮስና እንድርያስ ኢየሱስን የተከተሉት ምናቸውን ትተው ነበር?
- ጴጥሮስና እንድርያስ የኢየሱስ ተከታዮች የመሆን ጥልቅ ፍላጎታቸውን የገለፁት እንዴት ነበር?
- ኢየሱስ ያገኛቸው ሌሎቹ ወንድማማቾች እነማን ነበሩ?
- ዮሐንስና ያዕቆብ ኢየሱስ በመጣበት ወቅት ምን እያደረጉ ነበር?
- ከእነርሱ በጀልባው ውስጥ የነበረው ማን ነበር?
- ይህን አረፍተ ነገር አሟሉ። "የኢየሱስ ተከታዮች የመሆን መሻት ካለን ቃሎቹን ______________________________ ____________________________________________።"

# *ሀ3 ታሪክ 2*

## ኢየሱስ ጴጥሮስን ረዳው። – ይህ ታሪክ ጴጥሮስ ምን ያህል ኃጢአተኛ እንደሆነ መማሩን የምናይበት ታሪክ ነው።

**በዚህ ክፍል የምንማራቸው የሚከተሉትን ነው።**

- የኢየሱስ ኃይል በጴጥሮስ ሕይወት ላይ ትልቅ ተፅእኖን አመጣ።
- ኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጅ ነው። ልክ ጴጥሮስ እንዳደረገው እኛም እንድንከተለው ይፈልጋል።

**ቁልፍ ጥቅስ** **ሉቃስ 5: 10**
**የጥናት ክፍል:** **ሉቃስ 5: 1 - 11**

### *መግቢያ*

- ልጆች በሚገባ ማድረግ የሚችሏቸውን ነገሮች እንዲያስቡ ጠይቋቸው። ሁላችንም ክህሎቶችና ችሎታዎች እንዳሉን ልጆችን አሳስቧቸው።
- ጴጥሮስ ጥሩ አሳ አጥማጅ ነበር። ለረጅም ጊዜ አሳ አጥማጅ ነበር። ሆኖም በዛሬው ታሪክ ጴጥሮስ እንዲሳካለት የኢየሱስን *መመሪያ መታዘዝ እንደሚያስፈልገው ተማረ።* (ጴጥሮስ አንዳንዴ ስምዖን ወይንም ስምዖን ጴጥሮስ ተብሎ እንደሚጠራ ልታብራሩላቸው ያስፈልግ እንደሆነ አስቡ።)

### የማስተማር ጊዜ

- ልጆች ባለፈው ታሪክ የነበረውን መቼት እንዲያስታውሱ አድርጓቸው። በዛሬው ታሪክ ኢየሱስ የጴጥሮስን ጀልባ ተጠቅሞ ሕዝቡን ከእግዚአብሔር ቃል አስተማራቸው። (**ሉቃስ** 5: 1 – 3)
- ኢየሱስ ለጴጥሮስ የሰጠው ትዕዛዝ። ኢየሱስ ጴጥሮስን መረቡን ወደ ጥልቁ እንዲጥልና አሳ እንዲያጠምድ ነገረው። (**ሉቃስ** 5: 4 -5) *በዚህ ጉዳይ የጴጥሮስ ስሜት ምን እንደነበር ለማየት ሞክሩ።*
- ትልቁ የተጠመደ የአሳ መጠን (**ሉቃስ** 5: 6, 7) *በሌሊቱ ርዝማኔ የሆነውንና የአሁኑን የተያዘ የአሳ መጠን አነፃፅሩ። ይህ ተአምር ነበር! የአሶች ፈጣሪ በጴጥሮስ መርከብ ውስጥ ነበር። ወደ ጴጥሮስ መረብ አሶቹን ያመጣቸው የፈጣሪያቸው ኃይል ነበር።*
- የጴጥሮስ ምላሽ (**ሉቃስ** 5: 8 - 9) የኢየሱስን ማንነት በተመለከተ ለጴጥሮስ አዲስ መገለጥ እንደመጣለት ለልጆቹ አስረዷቸው። ጴጥሮስ ኢየሱስ እንደእርሱ ተራ ሰው እንዳልነበር ተረዳ። ኢየሱስ ሁሉን የሚችል ጌታ እንደሆነና ጴጥሮስ ራሱን ከኢየሱስ ጋር ሲያወዳድረው ኃጢአተኛ እንደሆነ ተገነዘበ።
- የጴጥሮስ አዲሱ ስራ (**ሉቃስ** 5: 10) ኢየሱስ ከአሁን ጀምሮ ሰዎችን አጥማጅ እንደሚሆን ነገረው! *ልጆች ባለፈው ሳምንት ታሪክ ውስጥ የተጠቀሰውን ይህንኑ ሀሳብ ተረድተው እንደሆነ አረጋግጡ።* አሁን ጴጥሮስ አንድ ነገር ተረዳ። ይህም ኢየሱስ ክርስቶስ የላቀ ስራ እንዳሰበለትና ሁሉን ነገር ትቶ ኢየሱስን የሚከተልበት ጊዜ መሆኑን ነው። (**ሉቃስ** 5: 11)
- *ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ የእርሱን ታላቅነትና ኃይሉን እንድረዳ ይፈልጋል። በሕይወታችን እንዲኖር ማድረግ እንችላለን። እንደጴጥሮስ ልንከተለውና ልንታዘዘው ስንወስን በሕይወታችን ትልቅ ለውጥ ይከተላል።*

**የዘመነ መጽሐፍ ቅዱስ ትምህርቶችን አጠናቁ።**

### *የመማር ጊዜ*

እንደአስፈላጊነቱ የመጽሐፍ ቅዱስ ቁልፍ ጥቅሶችን አብራሩ፣ አስተምሩ። - **ሉቃስ** 5: 10

### የክለሳ ጊዜ

- ኢየሱስ የተጠቀመበትና የጴጥሮስ የሆነ ነገር ምንድ ነበር?
- ኢየሱስ ሕዝቡን ካስተማረ በኋላ ጴጥሮስን ምን እንዲያደርግ አዘዘው?
- ጴጥሮስ ለመጨረሻ ጊዜ አሳ ያጠመደው መቼ ነበር?
- ካጠመደው የአሳ መብዛት የተነሳ ጴጥሮስ ያደረገው ምን ነበር?
- ኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጅ ስለሆነ ሊያደርግ የሚችለው ልዩ ነገር ምንድ ነው?
- ኢየሱስ በጌታ በኢየሱስ እግር ስር የተንበረከከው ለምን ነበር?
- በተያዘው የአሳ ብዛት የተደነቀው ማን ነበር?
- ኢየሱስ ጴጥሮስን ከዚህ በኋላ ምን ታደርጋለህ አለው?
- ከዚህ ታሪክ ፍፃሜ በኋላ ጴጥሮስና ባልንጀሮቹ ምን አደረጉ?

**ማሳየት** እርሳስ፣ ወረቀትና መቀስ ባለበት በት/ቤት አውድ የምታስተምሩ ከሆነ እያንዳንዱ ልጅ የአሳ ስዕል ሰርቶ በቅርፁ ቆርጦ እንዲያወጣው አድርጉ። ሁሉም አሶች በአንድነት የሚታዩበት ቦታ አዘጋጁ። ከዚያም ርዕስ ስጡት። ርዕሱ ***"ጴጥሮስ ብዙ አሳ እንዲያጠምድ ኢየሱስ ሲረዳው"*** የሚል ሊሆን ይችላል።

## ሀ3 ታሪክ 3

## ኢየሱስ ማዕበሉን ፀጥ እንዲል አደረገው። – ይህ ታሪክ ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ ኃይል የሚያወሳ ታሪክ ነው።

| | |
|---|---|
| | **በዚህ ክፍል የምንማራቸው የሚከተሉትን ነው።**<br>• ኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጅ ስለሆነ ማዕበሉን ፀጥ አደረገው።<br>• እኛም ኢየሱስ ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ እንደሆነ ማመን አለብን።<br><br>**ቁልፍ ጥቅስ** ***ማቴዎስ* 8: 27**<br>**የጥናት ክፍል:** ***ማቴዎስ* 8: 23 – 27** |
| *መግቢያ* | • ልጆቹ ሊረዱት በሚችሉበት መልክ በዚህ ታሪክ ውስጥ ስለ ተገለፀው የአየር ሁኔታ ተነጋገሩ። የአየር ሁኔታ ወዲያውኑ ሲለወጥ አይታችሁ ታውቃላችሁ? ለምሳሌ ያህል ከባድ ዝናብ በድንገት ቢዘንብባችሁ አስቡ።<br>• ኃይለኛ ንፋስና ከባድ የአየር ሁኔታ እንዴት በጀልባ መቅዘፍን አስቸጋሪ እንደሚያደርጉት አውሩ። በዛሬው ታሪክ ኢየሱስና ደቀ መዛሙርቱ የገሊላ ባሕርን በጀልባ እየቀዘፉ በማቋረጥ ላይ ናቸው። |
| የማስተማር ጊዜ | • ***መረጋጋት ጀመረ።*** የነበረውን የተረጋጋ ሁኔታ አስረዷቸው። ኢየሱስ ወዲያው እንቅልፍ ስለ ያዘው ተኛ። (**ማቴዎስ 8: 23, 24**)<br>• ***ማዕበሉ።*** በድንገት እጅግ በጣም አስፈሪ ማዕበል ተነሳ። ደቀ መዛሙርቱ እጅግ በጣም ፈሩ። (**ማቴዎስ 8: 24**) ይህን ሁኔታ በሚታይ መልኩ ግለፁት – አስፈሪውን የማዕበል ድምፅ፣ ወደ ጀልባይቱ እየገባ ያለውን ውኃ፣ ከዚህ ለማምለጥ እየተደረገ ያለውን ሙከራ....<br>• ***የደቀ መዛመርቱ ፍርሃት።***<br>ሊሰጥሙ እንደሚችሉ በማሰብ ደቀ መዛመርቱ እጅግ በጣም ደነገጡ። ፈጥነው ኢየሱስን ከእንቅልፉ ቀሰቀሱትና እንዲያድናቸው ለመኑት። ይህን ልመና ለማቅረብ የተጠቀሙባቸውን ትክክለኛ ቃላት ተጠቀሙ። (**ማቴዎስ 8:25**) ደቀ መዛመርቱ በእርሱ ላይ እምነት ስላልነበራቸው ኢየሱስ ቅር ተሰኘባቸው። እምነት ማለት ኢየሱስ ከምንም ነገር ሊያድነን እንደሚችል መረዳት ማለት ነው። (**ማቴዎስ 8: 26ሀ**)<br>• ***የኢየሱስ ኃይል***<br>ኢየሱስም ማዕበሉን ፀጥ እንዲል አደረገው። ማዕበሉም ቆመ። (**ማቴዎስ 8:26ለ**) በተጨማሪም **ማርቆስ 4: 39**ን አንብቡ። *ማዕበሉ ወዲያውኑና ሙሉ በሙሉ መቆሙን አፅንኦት ሰጥታችሁ ግለፁላቸው።*<br>• የደቀ መዛሙርቱ አድናቆት (**ማቴዎስ 8: 27**)<br>*ደቀ መዛመርቱ ኢየሱስ በንፋሱና በማዕበሉ ላይ ያለውን ኃይል ሲያዩ ከእነርሱ ልዩ እንደሆነ መገንዘባቸውን አስረዷቸው።*<br>• *ኢየሱስ ለምን ማዕበሉን ፀጥ እንዲል እንዳደረገ ልጆቹ ተረድተው እንደሆነ አረጋግጡ። ሁሉን የፈጠረ የእግዚአብሔር ልጅ ነው።*<br>• *በአለም ውስጥ በሚገኙ በሁሉም ነገሮች ላይ ስልጣን አለው። ይህም የአየር ፀባዮችንና የአየር ሁኔታዎችን ይጨምራል። ልጆች በሕይወታቸው በሚያጋጥሟቸው ችግሮች ሁሉ በኢየሱስ መታመን እንዳለባቸው እንዲሁም ኢየሱስ በየትኛውም ጊዜ የሁሉም የበላይ እንደሆነ እንዲገነዘቡ አበረታቷቸው።*<br>• *ኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጅ እንደሆነ በእውነት ልናምን ይገባናል።*<br>**የዘመነ መጽሐፍ ቅዱስ ትምህርቶችን አጠናቁ።** |
| የመማር ጊዜ | እንደአስፈላጊነቱ የመጽሐፍ ቅዱስ ቁልፍ ጥቅሶችን አብራሩ፣ አስተምሩ። - **ማቴዎስ 8: 27** |
| የክለሳ ጊዜ | • ይህ ታሪክ የተከናወነው የት ነበር?<br>• ጀልባው ውስጥ መጀመሪያ የገባው ማን ነበር?<br>• ማዕበሉ ሲመጣ ውኃው ምን ሆነ?<br>• ማዕበሉ ሲጀምር ኢየሱስ ምን እያደረገ ነበር?<br>• ደቀ መዛመርቱ ኢየሱስን ከእንቅልፉ የቀሰቀሱት ለምን ነበር?<br>• ኢየሱስ በደቀ መዛመርቱ ለምን ቅር ተሰኘ?<br>• ኢየሱስ ያስቆማቸው ሁለት ነገሮች ምን ነበረ?<br>• ቁልፍ ጥቅሱ የትኛው ነው?<br>• ኢየሱስ ማዕበሉን ማስቆም የቻለው ከደቀ መዛመርቱ ግን አንዳቸውም ያን ማድረግ ያልቻሉት ለምን ነበር?<br>• ኢየሱስ ላደረገው አስገራሚ ነገር የተሰጠው ስያሜ ምን ነበር?<br><br>ይህ ትረካ ከድራማ ጋር ተቀራራቢነት ያለው ትረካ ነው። በጀልባ ተምሳሌት በተሰራ አንድ ነገር ላይ የተቀመጡ 12 ደቀመዛሙርት አሉበት። ሌሎች ደግሞ በማዕበሉ ምክንያት የተፈጠረውን ድምፅ ያሰማሉ። በመካከላቸው ያለ አዋቂም ልክ ከልጆቹ እንቅስቃሴ ጋር አብሮ በሚሄድ መልኩ ታሪኩን ያነባል። |

# <u>ሀ3 ታሪክ 4</u>
## ኢየሱስ ጴጥሮስን አዳነው። – ይህ ታሪክ የጴጥሮስ አጭር ፀሎት ነው።

| | |
|---|---|
| | **በዚህ ክፍል የምንማራቸው የሚከተሉትን ነው።**<br>• ኢየሱስ የጴጥሮስን አጭር ፀሎት ሰምቶ አዳነው።<br>• ለመዳን በኢየሱስ ክርስቶስ መታመን ይገባናል።<br><br>**ቁልፍ ጥቅስ** **ማቴዎስ** 14: 33<br>**የጥናት ክፍል:** **ማቴዎስ** 14: 22 - 33 |
| *መግቢያ* | • ከሰዎች ጋር አብረን የምናሳልፈው ጊዜ በጨመረ ቁጥር ይበልጥ እያወቅናቸው እንሄዳለን። ጴጥሮስ ከኢየሱስ ጋር በነበረው የእስካሁን ቆይታው ምን እንደተማረ ለልጆች አስረዳቸው።<br>• ሀሳቦቻቸውን ያቅርቡ። እናንተም በተገላጭ ቻርት *(የተገላጭ ቻርት ካለ)* ላይ የሚያቀርቧቸውን ሀሳቦች ፃፉላቸው። ከመልሶቻቸው መካከል የሚከተሉት ሊገኙባቸው ይችላሉ። (ኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጅ እንደሆነ፣ ተአምራትን ማድረግ እንደሚችል፣ በባሕሩ ላይ ስልጣን እንዳለው ወዘተ...)<br>• ዛሬ በምናየው ታሪክ ጴጥሮስ ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ ይበልጥ እንደተማረ እናያለን። |
| የማስተማር ጊዜ | • ኢየሱስ በግሉ ለፀሎት በሄደበት ወቅት ደቀ መዛመርቱ ደግሞ በጀልባ እየቀዘፉ በባሕር ላይ ነበሩ። (**ማቴዎስ** 14: 22 – 23) *በኢየሱስ ሕይወት የፀሎትን አስፈላጊነት አስረዷቸው።*<br>• **ማዕበሉ።** (**ማቴዎስ** 14: 24)<br>*ባለፈው ሳምንት የተመለከትነውን የማዕበሉን ታሪክ እንደገና አንሱት። የአሁኑን ደግሞ አብራሩት።* ኢየሱስ ደቀ መዛመርቱ ችግር ላይ መሆናቸውን ስላየ በእኩለ ሌሊት በባሕር ላይ እየተራመደ መጣ። (**ማቴዎስ** 14: 25 – 27) *ደቀ መዛመርቱ ምን በማሰብ ላይ እንደነበሩና ምን እንደተሰማቸው አስረዱ። የኢየሱስን የማበረታቻ ቃላት አብራሯቸው።*<br>• **የጴጥሮስ ልመና።**<br>ጴጥሮስ ኢየሱስ መሆኑን ማረጋገጥ ፈለገ። ስለዚህ ኢየሱስን ልክ እንደእርሱ በውኃ ላይ መራመድ እንዲችል ጠየቀው! ኢየሱስም ጴጥሮስን "ና!" አለው። ስለዚህም ጴጥሮስ ከጀልባው ውስጥ ወጥቶ ወደ ኢየሱስ መራመድ ጀመረ። (**ማቴዎስ** 14: 28 – 29) ጴጥሮስ አይኖቹን ከኢየሱስ ላይ እስከሚነቀልና የውኃውን ማዕበል እስከሚያይና እከስሚገነዘብ ድረስ ሁሉም ነገር ልክ ነበር። አሁን መስጠም ጀመረ!<br>• **ኢየሱስ ጴጥሮስን አዳነ።**<br>• *ጴጥሮስ ልክ መስጠም ሲጀምር ኢየሱስ እንዲያድነው ሲጣራ እናነባለን። በዚህን ጊዜ ጴጥሮስ የተናገራቸውን ትክክለኛ ቃላት ተጠቀሙ።.* (**ማቴዎስ** 14: 30 – 32) ከዚያም ጴጥሮስና ኢየሱስ በጀልባ ውስጥ ቆሙ። ማዕበሉም ፀጥ አለ። *ከሆነው ነገር የተነሳ የሌሎች ደቀመዛሙርትና የጴጥሮስ አድናቆትና ምላሽ ምን እንደሚመስል አብራሩላቸው።* (**ማቴዎስ** 14: 35)<br>• *ጴጥሮስ ከመስጠም መዳንን እጅግ ፈለገ። እኛም በሕይወታችን ካለ ኃጢአት መዳን አለብን። ለእኛ ያን ሊያደርግልን የሚችለው ኢየሱስ ክርስቶስ ብቻ ነው። ኢየሱስ በመስቀል ላይ በመሞት የእኛን ቅጣት ወሰደ። ልንታመነው ይገባናል።*<br><br>**የዘመነ መጽሐፍ ቅዱስ ትምህርቶችን አጠናቁ።** |
| *የመማር ጊዜ* | ቁልፍ ጥቅሱን እያብራራችሁ አስተምሩት። - **ማቴዎስ** 14: 33<br>*አምልኮ ምን ማለት እንደሆነ አብራሩ። ደቀመዛሙርት ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ በተማሩትና ባወቁት ነገር ምክንያት እጅግ ተደነቁ ከመጠን በላይም ደስተኞች ሆኑ። በሁሉም ስፍራ ለሚገኙና ኢየሱስን ለሚወዱ ሰዎች ይህ ከልባቸው ሊሉት የሚገባ አረፍተ ነገር እንደሆነ አብራሩላቸው።* |
| የከለሳ ጊዜ | ይህ የሙከራ ጥያቄ በሀ3 ታሪክ ውስጥ በሚገኙ ታሪኮች ላይ የተመሠረተ ሊሆን ይችላል። ካርዶች ካሏችሁ የተለያየ መጠን ያሏቸውን አሶች ማሳየት ትችላላችሁ። ልጆች አንድ ጥያቄ ሲመልሱ ከፊት ለፊት ከሚታዩት አሶች መካከል ይመርጣሉ ወይንም ደግሞ ይይዛሉ። እያንዳንዱ አሳ በላዩ ላይ የተለያዩ ነጥቦች ተመዝግበውበታል። ሁለት ቡድኖች ነጥቦቹን ለእያንዳንዳቸው እንዲደምሩ አድርጉ።<br>• እነኚህ ታሪኮች ሁሉ የተፈፀሙት የት ነበር?<br>• "ከእኔ በኋላ ኑ። እኔም ______________________________ አደርጋችኋለሁ።" የሚለውን አርፈተ ነገር አሟሉ።<br>• እነኝህን ቃላት ኢየሱስ የተናገረው ለማን ነበር?<br>• ጴጥሮስ የተያዘውን የአሳ ብዛት ሲያይ ምን አደረገ?<br>• በእውነት ______________________________ ብለው ሰገዱለት።<br>• ኢየሱስ ወደ ተራራ ላይ የወጣው ለምንድ ነበር?<br>• ደቀመዛሙርት እንዲፈሩ ያደረጋቸው ምንድ ነበር?<br>• ጴጥሮስ በዚህ ታሪክ ውስጥ ስለ ኢየሱስ የተማረው ምን ነበር? |

## *ሀ4 ታሪክ 1*

## ጴጥሮስ አንቀላፋ። ይህ ታሪክ ኢየሱስ ወደ አባቱ ስላደረገው ፀሎት ያወሳል።

**በዚህ ክፍል የምንማራቸው  የሚከተሉትን ነው።**

- በጌታ በኢየሱስ ሕይወት ፀሎት እጅግ አሰፈላጊ እንደነበረ እንማራለን።
- ለእኛም ፀሎት አስፈላጊ ነው።

**ቁልፍ ጥቅስ** ዮሐንስ 15: 14
**የጥናት ክፍል:** **ማቴዎስ** 26: 36-46

### *መግቢያ*

- ልጆች የሚያስቸግሯቸውን ነገሮች አንስታችሁ አውሩ። ለምሳሌ የረጅም ሩጫ የመጨረሻ ዙር፣ ለረጅም ጊዜ በአትኩሮት ማዳመጥ፣ አንድ ልዩ የሆነ ዝግጅትን ለመከታተል ሳይተኙ መቆየት።
- በዛሬው ታሪክ ኢየሱስ ከወዳጁ ከጴጥሮስ ልዩ የሆነ እርዳታ እንደፈለገ እናያለን። ኢየሱስ ጴጥሮስ እንዲያደርግለት የፈለገውን ነገር ማድረግ አለማድረጉን እናያለን።

### የማስተማር ጊዜ

- *የዚህን ታሪክ አውድ አስረዷቸው።* ኢየሱስ በመስቀል ላይ የሚሞትበት ጊዜ እየተቃረበ እንደሆነ አውቋል። ከደቀ መዛመርቱ ጋር በአንድነት የመጨረሻውን እራት በልቷል። ኢየሱስ በአባቱ ፊት ዘወትር ይፀልይ ነበር። አሁን ደግሞ ከፊት ለፊቱ ከሚጠብቀው መከራ የተነሳ መፀለይ ምን ያህል አስፈላጊ እንደሆነ ተገንዝቧል። መፀለይ ወደ ሚችሉበት ቦታ ከቀመዛሙርቱ ጋር አብሮ መጣ። በዚህ ምሽት ሶስቱን ልዩ ወዳጆቹ ከእርሱ ጋር አብረው እንዲተጉና እንዲፀልዩ በመፈለግ ከሌሎቹ ደቀ መዛመርቱ ጴጥሮስ፣ ያዕቆብና ዮሐንስ ለይቶ አብረውት እንዲሆኑ አድርጓል።
- ኢየሱስ ጴጥሮስ፣ ያዕቆብና ዮሐንስ ነቅተው እንዲፀልዩ አዘዛቸው። (**ማቴዎስ** 26: 36 – 37) ከዚያም ኢየሱስ ትንሽ ፈንጠር ብሎ ሄዶ ወደ አባቱ ፀለየ። *ኢየሱስ ምን ተሰምቶት እንደነበር አብራሩላቸው። ፀሎቱ እግዚአብሔርን በሁሉም ነገር ለማስደሰት መሻቱ እንደሆነ ያሳያል።* (**ማቴዎስ** 26: 38 – 39) ከአንድ ሰአት በኋላ ኢየሱስ ጴጥሮስና ሌሎቹ ሁለቱ ደቀመዛሙርት ተኝተው አገኛቸው። *እንዴት እንዳዘነ አውሩ።* (**ማቴዎስ** 26: 40 – 41)
- ኢየሱስ ለሁለተኛ ጊዜ ፀለየ። ወዳጆቹን ግን አሁንም ተኝተው አገኛቸው። (**ማቴዎስ** 26: 42 – 43)
- ኢየሱስ ለሶስተኛ ጊዜ ፀለየ። ተመልሶ ሲመጣም ተኝተው አገኛቸው። *ጴጥሮስና ሌሎቹ ደቀመዛሙርት እንዴት ኢየሱስን እንዳሳዘኑት ተወያዩ። በዚህ አስቸጋሪ ጊዜ ስለ ራሳቸው መፀለይ ሲገባቸው አልፀለዩም።* (**ማቴዎስ** 26: 44 – 45)
- በዚያን ጊዜ ጠላቶቹ ኢየሱስን ሊይዙት መጡ። (**ማቴዎስ** 26: 45 – 46)
- *በማጠቃለያ ፀሎት ከእግዚአብሔር ብርታት የምናገኝበት ምንጫችን እንደሆነና ፈተናን ማሸነፊያ መሳሪያችን እንደሆነ አስረዷቸው። ልጆች የሚያውቋቸውን ምሳሌዎች በዚህ ጊዜ መጥቀስ ይቻላል።*
- *ጴጥሮስና ሌሎቹ ደቀመዛሙርት ኢየሱስ እንዲተጉና እንዲፀልዩ የሰጣቸውን ትዕዛዝ መፈፀም አልቻሉም። ኢየሱስ እኛ ትዕዛዛቱን እንድናደርግ ይፈልጋል።*
- *ደቀ መዛመርቱ ካደረጉት ጋር ሲነፃፀር ኢየሱስ እኛን በፍፁም አይተወንም፣ አያሳዝነንም። ኢየሱስ በመፀለዩ ወደ መስቀል በመሄድ ስለ እኛ ሕይወቱን መስጠት የሚያስችለው ብርታት ከእግዚአብሔር ዘንድ ተቀበለ።*

**የዘመነ መጽሐፍ ቅዱስ ትምህርቶችን አጠናቁ።**

### የመማር ጊዜ

ቁልፍ ጥቅሱን እያብራራችሁ አስተምሩት። - **ዮሐንስ** 15: 14. የኢየሱስ ወዳጅ መሆን መታደል መሆኑን ልጆቹ እንዲገነዘቡ እርዷቸው።

### የክለሳ ጊዜ

- ኢየሱስ የፀለየው የት ነበር?
- ከእርሱ ጋር አብረው እንዲፀልዩ የመረጣቸው ደቀመዛሙርት እነማን ነበሩ?
- ኢየሱስ የፀለየው ስለ ምን ጉዳይ ነበር?
- ኢየሱስ ሲፀልይ ምን ስሜት ይሰማው ነበር?
- ኢየሱስ ለመጀመሪያ ጊዜ ያደረገው ምን ነበር?
- ደቀ መዛመርቱ መፀለይ ያልቻሉበት ምክንያት ምን ነበር?
- ኢየሱስ እንዲፀልዩ የጠየቃቸው ለምን ያህል ጊዜ ነበር?
- ኢየሱስ ፀሎቱን ሲፈፅም ምን ሆነ?
- ቁልፍ ጥቅሱ የሚገኘው የት ነው?
- ኢየሱስን ብንታዘዘው ምን ብሎ ይጠራናል?

<u>*ሀ4 ታሪክ 2*</u>

**ጴጥሮስ ሲዋጋ – ይህ ታሪክ ኢየሱስ ትዕዛዝ ሲያስተላልፍ ምን እንደሆነ የሚናገር ታሪክ ነው።**

**በዚህ ክፍል የምንማራቸው የሚከተሉትን ነው።**

- ኢየሱስ ጠላቶቹ እንዲይዙትና እንዲገድሉት ፈቀደ። .
- በጣም አስቸጋሪ በሆኑ ሁኔታዎች ውስጠ ቁጣችንን መቆጣጠር እንችላለን።

**ቁልፍ ጥቅስ** **ኤፌሶን** 4: 26

**የጥናት ክፍል:** **ማቴዎስ** 26: 47 - 56

### *መግቢያ*

በአትክልት ስፍራው ምን እንደሆነ ካለፈው ታሪክ መለስ ብላችሁ እዩ። ጴጥሮስና ጓደኞቹ ኢየሱስ እንደጠየቃቸው አልፀለዩም። ከፊት ለፊታቸው አስቸጋሪ ጊዜ እየመጣ ነው። ለመሆኑ ምን ያደርጉ ይሆን?

### የማስተማር ጊዜ

- የዚህን ገጠመኝ ትዕይንት አዘጋጁ። ጨለማና ጭር ያለ ምሽት ነበር። ሆኖም በድንገት የብዙ የታጠቁ ወታደሮች ከባድ የኮቴ ድምፅ ተሰማ። አሁን ጴጥሮስና ጓደኞቹ ምን የሚሰማቸው ይመስላችኋል?
- በድንገትም ከመጣው ሕዝብ መካከል ይሁዳ ወጣ ብሎ ወደ ኢየሱስ ቀረበና ኢየሱስን ሳመው። *ይሁዳ ማን እንደነበር አስረዷቸው። እንዲሁም ኢየሱስን የሳመው ወታደሮቹ ኢየሱስ የትኛው እንደሆነ ማወቅ የሚችሉበት ምልክት እንዲሆናቸው ፈልጎ እንደሆነም አስረዷቸው። "አሳልፎ መስጠት" ማለት ምን ማለት እንደሆነ ግለፁላቸው። (ደረጃ 2 የመጽሐፍ ቅዱስ ጊዜን እዩ።)* (**ማቴዎስ** 26: 47 – 50)
- ጴጥሮስ ኢየሱስ እንደተያዘ ሲረዳ እጅግ በጣም ተቆጣ። ስለዚህ ሊይዘው ከመጣው ሕዝብ መካከል አንደኛውን በመምታት ኢየሱስን ለማዳን ጥረት አደረገ። (**ማቴዎስ** 26: 51) *ልክ እንደ ጴጥሮስ ስሜታችንን መቆጣጠር ሊሳነንና በቀላሉ ልንቆጣ እንችላለን። በተመሳሳይ ሁኔታ በቀላሉ ስሜታችንን ሊያነሳሱ የሚችሉ ሁኔታዎችን በቡድኑ ውስጥ ካሉ ልጆች ጋር በአንድነት አቅርቡ። ኢየሱስ ጴጥሮስ ስለ እርሱ እንዲዋጋለት ፍላጎቱ እንዳልነበር አብራሩላቸው። ለዚህም ምክንያቱ በሕይወቱ አሁን እየሆነ ያለው በሙሉ የእግዚአብሔር ሀሳብና እቅድ ስለ ሆነ ነበር። ኢየሱስ ጠላቶቹ እንዲይዙትም ሆነ እንዲገድሉት ፈቃደኛ ነበር። ስለ እኛ ሲል በሞት ለማለፍ ወደደ። በኢየሱስና በጴጥሮስ መካከል ያለውን ልዩነት አሳዩአቸው።* ኢየሱስ ከመፀለዩ የተነሳ የተረጋጋ ነበር። ጴጥሮስ ካለመፀለዩ የተነሳ የመሰለው ኢየሱስ ስለ እርሱ እንዲዋጋለት ነበር። (**ማቴዎስ** 26: 52 – 56)
- ሌሎች የደነገጡ ደቀመዛመርት ኢየሱስን ትተውት ሄዱ። ይህ ለምን ሊሆን እንደቻለ ተወያዩበት። (**ማቴዎስ** 26: 56b) ለመከተል የሞከረው ጴጥሮስ ብቻ ነበር። ያም ቢሆን ራቅ ብሎ እንጂ ትኩረትን ሊስብ በሚችል መጠን አልነበረም። *የምታስተምሯቸው ልጆች ጴጥሮስ ሳይታወቅበት ይህን እንዴት ማድረግ እንደሚችል ማየት እንዲችሉ እርዷቸው።* (**ማቴዎስ** 26: 58)
- *እኛም የኢየሱስ ክርስቶስ ከሆንን ቁጣ እንዳይቀድመን ሆኖም ራሳችንን መግዛት እንድንችል ወደ እርሱ መፀለይና ጥያቄ ማቅረብ እንችላለን። በአማኝ ሕይወት ውስጥ የሚኖረው መንፈስ ቅዱስ ትክክለኛ ባሕርይ እንዲኖረው ይረዳዋል።*
- *ባንቆጣና ባንደባደብ በሰላም ሊጠናቀቅ ስለ ሚችል አንድ ሁኔታ አውሩ።*

**የዘመነ መጽሐፍ ቅዱስ ትምህርቶችን አጠናቁ።**

### የመማር ጊዜ

ቁልፍ ጥቅሱን እያብራራችሁ አስተምሩት። - **ኤፌሶን** 4:26. ቁጠኞች ከሆንን ይህን በአሰቸኳይ ማስወገድ እንዳለብን ግለፁላቸው!

### የክለሳ ጊዜ

- ከኢየሱስ ጠላቶች ጋር አብሮ የመጣው ማን ነበር?
- ይሁዳ ኢየሱስን ለጠላቶች ያሳየው እንዴት ነበር?
- ኢየሱስ ሲያዝ ጴጥሮስ ምን ይዞ ነበር?
- ጴጥሮስ የሰውየውን የትኛውን የሰውነት ክፍል የቆረጠው ነበር?
- ኢየሱስ ጴጥሮስን ምን እንዲያደርግ አዘዘው?
- ክርስቲያን ቁጣን እንዴት ነው የሚያሸንፈው?
- ኢየሱስ ሲያዝ ደቀ መዛመርቱ ምን አደረጉ?
- በርቀት ኢየሱስን ለመከተል የሞከረው ማን ነበር?

**ተውኑት :** መሪዎች አንድ ሰው ሲቆጣ የሚያሳይ አንድ ወይንም ከዚያ በላይ የሆኑ ትዕይንቶችን ማሳየት ይችላሉ።

<u>ሀ4 ታሪክ 3</u>

## ጴጥሮስ ኢየሱስን ካደው። – ይህ ታሪክ ይቅርታ ስለ ማግኘት ይተርካል።

<table>
<tr><td></td><td>በዚህ ክፍል የምንማራቸው የሚከተሉትን ነው።<ul><li>አንዳንድ ጊዜ ስንፍናችን ወዳጆቻችንን ሊያሳዝናቸው ይችላል።</li><li>ኢየሱስ ክርስቶስን ስንበድለው ይቅር ሊለን ፈቃደኛ ነው።</li></ul>ቁልፍ ጥቅስ መዝሙር 51: 7<br>የጥናት ክፍል: ማቴዎስ 26: 69 – 75</td></tr>
<tr><td>መግቢያ</td><td><ul><li>ሰዎችን በድምፃቸው እንዴት እንደምንለያቸው ተነጋገሩ። ልጆች በስልክ ከሌሎች ጋር የማውራት እድሉ ገጥሟቸው ከሆነ በስልክ ከእነርሱ ጋር እያወራ ያለው ሰው ማን እንደሆነ ማንም ሳይነግራቸው ያውቃሉ። ቀበሌኛ የሰዎችን ድምፅ ይለያያል። በምትኖሩበት አካባቢ ያሉ ጥቂት ምሳሌዎችን መጥቀስ ትችላላችሁ። ለምሳሌ ያህል በአዲስ አበባ የሚነገር አማርኛና በጎንደር የሚነገር አማርኛ ልዩነት አለው።</li><li>ያለፈውን ታሪክ ለማስታወስ ሞክሩ። ኢየሱስ እንዴት እንተያዘና ደቀ መዛመርቱም እንዴት እንደሸሹ አስታውሷቸው። ጴጥሮስ ኢየሱስ ምን እየተፈፀመበት እንደሆነ ለማወቅ ፈለገ።</li></ul></td></tr>
<tr><td>የማስተማር ጊዜ</td><td><ul><li>ጴጥሮስ በሊቀ ካህናቱ ግቢ ውስጥ እስካለው የፍርድ ሸንጎ ድረስ ሄደ። (ማቴዎስ 26: 69ሀ) የፍርድ ሸንጎውም ከሊቀ ካህናቱ መኖሪያ ቤት ወጣ ያለ ነው። ከተቻለ ልጆቹ በሚገባ የሚያውቁትና የፍርድ ሸንጎ ያለውን ሕንፃ እንደምሳሌ ተጠቀሙ። ትዕይንቱን አስቡ። – ቀዝቃዛ ምሽት፣ በሸንጎው ውስጥ ያሉ ታጣቂዎችና ሎሌዎች ወዘተ...</li><li>አንዲት አገልጋይ ጴጥሮስን ለይታ አወቀችው። ለሌሎችም ከኢየሱስ ጋር እንደነበረ ነገረቻቸው። ጴጥሮስም አገልጋዪቱ የምትለውን እንደማያውቅ ተናገረ። (ማቴዎስ 26: 69ለ - 70) ጴጥሮስ እንደዋሸ ልጆቹ እንዲገነዘቡ እርዷቸው። በእርግጥም ከኢየሱስ ጋር ነበር ! ጴጥሮስ ለምን እንደዋሸ ተመራመሩ።</li><li>ጴጥሮስ ወደ መውጫ በሩ እንደደረሰ ሌላ አገልጋይ ሴት እንደገና ለይታ አወቀችው። አሁንም ኢየሱስን እንደማያውቀው ጴጥሮስ ተናገረ። (ማቴዎስ 26: 71 - 72) ደረጃ 2ን ለሚጠቀሙ ልጆች “መካድ” ምን ማለት እንደሆነ አብራሩላቸው።</li><li>ከጥቂት ጊዜ በኋላ አንድ ሌላ ሰው የጴጥሮስ ንግግር ልክ ኢየሱስን ሲከተሉት እንደነበሩ ሌሎች ሰዎች እንደሚመስል አስተያየት ሰጠ። (ጴጥሮስ ልክ እንደኢየሱስና እንደሌሎቹ ተከታዮቹ እርሱም የገሊላ ሰው ነበር። ይህን መረጃ በመግቢያው ከቀረበው ሀሳብ ጋር አዛምዱት።) ጴጥሮስ ለሶስተኛ ጊዜ ኢየሱስን በመካዱ እንዴት እንደተቆጣና ምን ያህል በውስጡ ፍርሃት እንደገባበት አብራሩላቸው።</li><li>ዶሮው ጮኸ። ጴጥሮስም ቀደም ብሎ ኢየሱስ የተናገረው ትዝ አለው። (ማቴዎስ 26: 34). ጴጥሮስ ለምን እንደተበሳጨ አስረዷቸው። (ማቴዎስ 26: 74ለ - 75)</li><li>ጴጥሮስ መሳሳቱን አስረዱ። የኢየሱስ ተከታይ መሆኑን ለመናገር የሚያስችል በቂ ድፍረት አልነበረውም። ይልቁንስ ብዙ ዋሸ። ሁላችንም እንሳሳታለን።</li><li>እኛም በምናደርገውና በምንናገረው ነገር ጌታ ኢየሱስን የምናሳዝንበት ጊዜ ቀላል አይደለም። ስንሳሳት ይቅር ሊለን ኢየሱስ ሁሌም ፈቃደኛና ዝግጁ ነው። ምክንያቱም በመስቀል ላይ ስለ ኃጢአታችን ሞቷልና ነው።</li></ul>የዘመነ መጽሐፍ ቅዱስ ትምህርቶችን አጠናቁ።</td></tr>
<tr><td>የመማር ጊዜ</td><td>ቁልፍ ጥቅሱን እያብራራችሁ አስተምሩት። - መዝሙር 51:7. ይህ ፀሎት እንደሆነ አብራሩ። ጌታ ኢየሱስ ኃጢአታችንን ይቅር እንዲለን ስንለምነው ከኃጢአታችን ሙሉ በሙሉ አጥቦ ያነፃናል። ልክ እንደበረዶም ነጭ ያደርገናል። ። አስፈላጊ ከሆነም በረዶ ምን እንደሆነ አስረዱ።</td></tr>
<tr><td>የክለሳ ጊዜ</td><td><ul><li>ጴጥሮስ የሚጠብቀው የት ሆኖ ነበር?</li><li>ጴጥሮስን ያናገረው የመጀመሪያው ሰው ማን ነበር?</li><li>ጴጥሮስ ኢየሱስን “አላውቀውም” ያለው ለስንት ጊዜ ያህል ነበር?</li><li>ለምንድነው ጴጥሮስ እንዲህ መዋሸት ያስፈለገው?</li><li>ዶሮ ሲጮኽ ጴጥሮስ የሰማው ለምን ያህል ጊዜ ነበር?</li><li>ዶሮው ሲጮኽ ጴጥሮስ ያስታወሰው ነገር ምን ነበር?</li><li>ጴጥሮስ ለምን አለቀሰ?</li><li>ጌተ ኢየሱስ ክርስቶስን ስናሳዝነው ምን ማድረግ አለብን?</li></ul></td></tr>
</table>

## ሀ4 ታሪክ 4

## የጴጥሮስ ፍቅር – ይህ ታሪክ ጴጥሮስና ኢየሱስ ስላደረጉት ውይይት የሚያወሳ ነው። .

| | |
|---|---|
| | **በዚህ ክፍል የምንማራቸው የሚከተሉትን ነው፡፡**<br>• ከክህደቱ በኋላ ጴጥሮስ ለኢየሱስ ክርስቶስ ያለውን ፍቅር ለመግለፅ ሌላ እድል እንደተሰጠው እንማራለን፡፡<br>• ጌታ ኢየሱስ እንድንወደው ይፈልጋል፡፡<br><br>**ቁልፍ ጥቅስ** 1 ዮሐንስ 4: 19<br>**የጥናት ክፍል:** ዮሐንስ 21: 1 - 19 |
| *መግቢያ* | • ልጆች ስለ ጴጥሮስ የሰሟቸውን የመጀመሪያ ታሪኮች እንዲያስታውሱ ጠይቋቸው፡፡ ጌታ ኢየሱስ ጴጥሮስን መጀመሪያ ሲጠራው ስራው ምን ነበር?<br>• ከዚያ በኋላ በርካታ ነገሮች እንደተከናወኑ አስረዱ፡፡ ጴጥሮስ ከኢየሱስ ክርስቶስ የቅርብ ጓደኞች መካከል አንደኛው ሆኖ ሳለ ኢየሱስን አሳዘነው፡፡ (የመጨረሻዎቹን ሶስት ታሪኮች አስታውሱ፡፡)<br>• ከጥቂት ጊዜ በኋላም ኢየሱስ በመስቀል ላይ ሞተ፡፡ ነገር ግን ከሞት ተነሳ፡፡ በሁለት የተለያዩ ጊዜያት ኢየሱስ ደቀ መዛሙርቱን ተገናኛቸው፤ ሕያው እንደሆነም አሳያቸው! ይህ ከሆነ በኋላ አንድ ቀን ጴጥሮስ ወደ አሳ ማጥመድ ስራው ለመመለስ ወሰነ፡፡ |
| የማስተማር ጊዜ | • ደቀ መዛመርቱ ሙሉ ቀን በአሳ ማጥመድ ስራ ሲደከሙ ቢያድሩም ምንም አሳ አልያዙም! (**ዮሐንስ 21: 3**) *ልጆቹ በዚህ አይነት ሁኔታ ውስጥ የነበሩት ደቀመዛሙርት ምን ሊሰማቸው እንደሚችል እንዲያስቡ አድርጓቸው፡፡ (ድካም፣ ረሃብ፣ ተስፋ መቁረጥ)*<br>• *የትዕይንቱን ስዕል በአእምሯቸው ለመቅረፅ እንዲችሉ አድርጉ፡፡ -የንጋቱን ፀሐይ፣ በባሕር ዳርቻው ላይ የቆመ ሰው ወዘተ... በእንግዳው ሰውና በደቀ መዛመርቱ መካከል እየተደረገ ያለውን ውይይት አንብቡት፡፡* (**ዮሐንስ 21: 4 – 6ሀ**)<br>• የዚህን እንግዳ ሰው ትዕዛዝ ሲፈፅሙ እጅግ ብዙ ቁጥር ያለው አሳ አጠመዱ፡፡ (153) ዮሐንስ ወዲያው ያ እንግዳ ሰው ኢየሱስ እንደሆነ ገባው፡፡ ጴጥሮስ ከደስታው የተነሳ ዘሎ ባሕር ውስጥ ገባ፡፡ ከዚያም ኢየሱስን ለመገናኘት ሄደ፡፡ (**ዮሐንስ 21: 7 –8**)<br>• ኢየሱስ ለደቀ መዛመርቱ ቁርስ አዘጋጀ፡፡ (**ዮሐንስ 21: 9 – 14**) *በባሕር ዳርቻ ቁርስ መብላት ምን እንደሚመስል እንዲሁም ምንም ሳይጠብቁት በመካከላቸው ኢየሱስ መገኘቱ እንዴት ድንቅ እንደሆነ እንዲያስቡ አድርጓቸው፡፡*<br>• ኢየሱስ ከቁርስ በኋላ ከጴጥሮስ ጋር ተነጋገረ፡፡ ኢየሱስ ጴጥሮስ ይወደው እንደሆነ ሶስት ጊዜ ጠየቀው፡፡ (**ዮሐንስ 21: 15 – 19**) *ይህ ለጴጥሮስ እንዴት አስፈላጊ እንደሆነ ንገሯቸው፡፡ ይህ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ጴጥሮስን ይቅር እንዳለውና ለልዩ አገልግሎት እያዘጋጀው እንደሆነ የሚያሳይ ነው፡፡ ለደረጃ 2 ልጆች አሁን ጴጥሮስ ለኢየሱስ ያለውን ፍቅር ለሶስት ጊዜ ያህል እንዴት እየገለፀ እንዳለ አብራሩላቸው፡፡ ይህንንም ሶስት ጊዜ ኢየሱስን ከመካዱ ጋር እያነፃፁሩ እንዲያደርጉት ጠይቋቸው፡፡*<br>• *ልጆቹ ለኢየሱስ ክርስቶስ ያላቸውን ፍቅር እንዲፈትሹት ጠይቋቸው፡፡*<br>• *ኢየሱስ ጴጥሮስን የጠየቀው ጥያቄ እንዴት ሊመልሱት እንደሚችሉ ጠይቋቸው፡፡ ኢየሱስ ሁላችንም እንድንወደውና እንድናገለግለው ይፈልጋል፡፡*<br>• *እግዚአብሔር ይወደናል፡፡ ይህንንም ያሳየን ልጁን ኢየሱስ ክርስቶስን እኛን እንዲያድነን በመላክ ነው፡፡ የእኛም ምላሽ መሆን ያለበት እርሱን ማፍቀር ነው፡፡*<br><br>**የዘመነ መጽሐፍ ቅዱስ ትምህርቶችን አጠናቁ፡፡** |
| *የመማር ጊዜ* | እንደአስፈላጊነቱ የመጽሐፍ ቅዱስ ቁልፍ ጥቅሶችን አብራሩ፣ አስተምሩ፡፡ - **1 ዮሐንስ 4: 19** |
| የክለሳ ጊዜ | • ኢየሱስ በዚያ ምሽት እስኪገለጥ ድረስ ጴጥሮስና ጓደኞቹ ለምን ያህል ጊዜ ነው በአሳ ማጥመዱ ተግባር የተሰማሩት?<br>• መረባቸውን በየትኛው በኩል ነው እንዲጥሉ የታዘዙት?<br>• ምን ያህል አሳ ያዙ?<br>• እንግዳው ሰው ኢየሱስ እንደሆነ መጀመሪያ ያወቀው ማን ነበር?<br>• ኢየሱስን ለመገናኘት መጀመሪያ የፈለገው ማን ነበር?<br>• ጴጥሮስ ዘሎ ውኃ ውስጥ ከመግባቱ በፊት ምን አደረገ?<br>• ቁርስ ያዘጋጀው ማን ነበር?<br>• ቁርስ መብላት ለምን አስፈለጋቸው?<br>• ኢየሱስ ጴጥሮስን ሶስት ጊዜ የጠየቀው ጥያቄ ምን ነበር?<br>• የዚህ ትምህርት ቁልፍ ጥቅስ የት ይገኛል?<br><br>**ተውኑት**: አንዳንዱ የዚህ ትረካ ክፍሎች ወደ ትወና ይመራል፡፡ (ለምሳሌ ያህል አሳ ማጥመድ፣ በባሕር ዳርቻ የቆመ እንግዳ ሰው ማስተዋል፣ ውኃ ውስጥ ዘሎ መግባት፣ በመረብ ውስጥ የተያዙ አሶችን ጎትቶ ማውጣት፣ አሶችን መቁጠር ወዘተ...) በፊት ገፅታ ላይ የሚነበቡ ስሜቶች (ለምሳሌ ያህል ቅሬታ፣ አድናቆት፣ ደስታ ወዘተ...) የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪኩን ለልጆች ማንበብና በተገቢው ቦታ ላይ ቀለል ያሉ የትወና ተግባራትን እንዲያከናውኑ ማድረግ ውጤታማ ነው፡፡ |

## ሀ5 ታሪክ 1

## አብርሃም የትውልድ ቦታውን ለቆ ወጣ። – ይህ ታሪክ አብርሃም እግዚአብሔርን ስለ መታመኑ ይናገራል።

| | |
|---|---|
| | **በዚህ ክፍል የምንማራቸው የሚከተሉትን ነው።**<br>• አብራም ከኡር ምድር ወጥቶ ወደ ሌላ ወደ ማያውቀው አዲስ ምድር ሲሄድ እግዚአብሔርን ታዘዘ።<br>• በእግዚአብሔር መታመናችንን የምናሳየው እግዚአብሔርን በመታዘዝ ነው።<br>**ቁልፍ ጥቅስ** **ዘፍጥረት** 3: 5<br>**የጥናት ክፍል:** **ዘፍጥረት** 12: 1-9 |
| *መግቢያ* | • ልጆች የተለማመዱት ነገር ከሆነ ቤት ስለ መቀየር አውሩ።<br>• ከትውልድ አገራቸው ርቀው በሌላ አገር መኖርን ሲያስቡ ምን ይሰማቸዋል? - ደስተኝነት? ጭንቀት? ሐዘን? ምክንያቶችን ይስጡ።<br>• አብራምን አስተዋውቁት። እንዲሁም በኡር ምድር ሕይወቱ ምን ይመስል እንደነበር ተናገሩ። (ቤተሰቡን፣ ጓደኞቹን፣ እንስሳቱን፣ ሀብቱን ....) በኡር ምድር ደስ የሚል ኑሮ ነበረው! |
| *የማስተማር ጊዜ* | • አንድ ቀን እግዚአብሔር አብራምን "የምትኖርበትን ምድር ትተህ እኔ ወደ ማሳይህ ምድር ሂድ።" አለው። (**ዘፍጥረት** 12: 1) *እግዚአብሔር አብራምን በጠየቀው ጥያቄ ውስጥ ከባዱ ነገር ምን ነበር? (በቤቱ ውስጥ የነበረውን መልካም ኑሮ መተውና የት እንደሚሄድ አለማወቁ)*<br>• እግዚአብሔር ለአብራም ቃል ገባለት። (**ዘፍጥረት** 12: 2-3) *የእግዚአብሔር የተስፋ ቃል ሁልጊዜም ቢሆን መልካም ነው። ለምሳሌ ትልቅ ሕዝብና ትልቅ ስም። እግዚአብሔር አብራምን መባረክ ፈለገ። እግዚአብሔር አብራምን መባረክ ሲፈልግ መልካምነቱን ያሳየዋል።*<br>• *አብራም እግዚአብሔርን ታዘዘ።* (**ዘፍጥረት** 12: 4) አብራም ለምን ታዘዘ ትላላችሁ? *(የእግዚአብሔርን የተስፋ ቃል አመነ፣ እግዚአብሔርን አመነ።)*<br>• *ከአብራም ጋር ማን እንደነበረ አስረዱ። – ሚስቱ ሳራ፣ የወንድሙ ልጅ ሎጥ፣ ሎሌዎቹ። እንዲሁም እግዚአብሔር በሚሄድበት መንገድ ሁሉ ከእርሱ ጋር ነበር። በምድረ በዳ እንዴት በግመሎች እንደተጓዙና በየቦታው ድንኳን ኢያበጁ እንደቆዩ አብራሩላቸው።*<br>• በመጨረሻም አብራም ከነአን ምድር ደረሰ። (**ዘፍጥረት** 12: 6–9)<br>• *አሁን አብራም ምን ይሰማዋል? መሰዊያን ማዘጋጀት እግዚአብሔርን ለማመስገን የሚጠቀምበት መንገድ ነበር።*<br>• *እግዚአብሔር እኛም እንድንታመንበት የሚፈልግባቸውን ጉዳዮች አንስታችሁ አውሩ።*<br>• *ይህ ማለት በእግዚአብሔር ሙሉ በሙሉ መታመን ማለት እንደሆነ አብራሩላቸው። በእግዚአብሔር ማመን ማለት እግዚአብሔር ነገሮችን ወደ ፍፃሜ እንደሚያመጣቸው ማመን እንጂ በራሳችን ችሎታ ወይንም መንገድ መመካት አለመሆኑን መረዳት አስፈላጊ ነው።*<br><br>**የዘመኑ መጽሐፍ ቅዱስ ትምህርቶችን አጠናቁ።** |
| *የመማር ጊዜ* | ቁልፍ ጥቅሱን እያብራራችሁ አስተምሩት። - **ምሳሌ** 3: 5. ይህ ጥቅስ አብርሃም ምን እንዳደረገ እንደሚናገር አስረዱ። – በሙሉ ልቡ በእግዚአብሔር አመነ እንጂ ነገሮችን በራሱ መንገድ እንዲሆኑለት አልጣረም። |
| *የክለሳ ጊዜ* | የመማር አላማው መሳካቱን ለመገምገም አዎ/አይደለም የሚሉ መልሶችን ለመመለስ የሚያስችሉ ጥያቄዎችን ጠይቋቸው።<br>• እግዚአብሔር አብራምን ተናገረው።<br>• አብራም የሚኖርበትን ምድር ለቆ የሄደው በድርቅ ምክንያት ነው።<br>• እግዚአብሔር አብራምን ለመባረክ ቃል ገባለት።<br>• አብራም ከአገሩ ሲወጣ እድሜው 70 ዓመት ነበር።<br>• አብራም ወዴት እንደሚሄድ ያውቅ ነበር።<br>• አብራም ሎጥ የሚባል ልጅ ነበረው።<br>• እግዚአብሔር አብራምን ወደ ከነአን ምድር መራው።<br>• አብራም በአዲሱ ምድር በቤት ውስጥ ኑሮ ጀመረ።<br>• አብራም በእግዚአብሔር መታኑን ያሳየው በመታዘዝ ነበር።<br>• እግዚአብሔር እኛ እንድንታዘዘውና እንድናምነው ይሻል። |

## *ሀ5 ታሪክ 2*

## አብራምና ሎጥ – ይህ ታሪክ ስለ ሎጥ በራስ ወዳድነት የተሞላ ምርጫ ይናገራል።

| | |
|---|---|
| | **በዚህ ክፍል የምንማራቸው የሚከተሉትን ነው።**<br>• ሎጥ በራስ ወዳድነት ላይ የተመሠረተ ምርጫ ስለ ማድረጉና ይህም ምርጫ ክፉ ምርጫ ስለ መሆኑ እንማራለን።<br>• ትክክለኛ ምርጫ ማድረግ በጣም አስፈላጊያችን እንደሆነ እንማራለን።<br>**ቁልፍ ጥቅስ** **ፊልጵስዩስ** 4: 19 or **ዘፍጥረት** 13: 15<br>**የጥናት ክፍል:** **ዘፍጥረት** 13: 1 - 18 |
| *መግቢያ* | • ልጆች ስለ ሚያደርጓቸው ምርጫዎች እንዲሁም በምርጫ ረገድ ለሌሎች ቅድሚያ ስለ መስጠት ተነጋገሩ። ከባህላችሁ ጋር ተዛምዶ ያለውን ልዩ ምሳሌ ምረጡ።<br>• ስለ መጋጨትና ግጭት እንዴት የሰዎችን ግንኙነት እንደሚያበላሽ ተነጋገሩ። |
| የማስተማር ጊዜ | • የአብራምና የሎጥ ሎሌዎች እንስሳቶቻቸውን ለግጦሽ በሚያሰማሩበት ስፍራ ምክንያት ተጋጩ። (**ዘፍጥረት** 13: 5–7)<br>• አብራም ግጭቱ መልካም እንዳልሆነ ስለ ተረዳ ሎጥ ለእንስሳቱ መምረጥ የሚፈልገውን የግጦሽ መሬት እንዲመርጥ ቅድሚያን ሰጠው። (**ዘፍጥረት** 13: 8–9)<br>• *የመሬቱን አቀማመጥ በስዕላዊ መልክ ለማሳየት እየሞከራችሁ ሎጥ ከፊት ለፊቱ ባለው የግጦሽ መሬቶች ምርጫ ላይ ንፅፅር ለማድረግ ሞክሩ። ይህም ለጥ ያለውን፣ በቂ የግጦሽ ሳርና በቂ ውኃ ያለውን የዮርዳኖስን ሸለቆ በኮረብቶች ከተከበበውንና ምንም ለምነት ከሌለው ምድር ጋር በማነፃፀር ይሁን። ሎጥ ምን የሚመርጥ ይመስላችኋል?*<br>• የሎጥ ምርጫ (**ዘፍጥረት** 13: 10–13) *ሎጥ ይህን ምርጫ ለምን አደረገ ትላላችሁ? (መልካም የሚመስለውን አየ። ለራሱ ለማድረግም ፈለገ።) ሎጥ ስግብግብነትና ራስ ወዳድነት ታየበት። ይህ እኛም ልናደርገው የምንችለው ነገር ነው። የሎጥ ምርጫ እርሱ እንዳሰበው መልካም ምርጫ አልነበረም። ምክንያቱም በዚያ ይኖሩ የነበሩ ሰዎች እግዚአብሔርን የሚያስደስቱ ሰዎች አልነበሩም።*<br>• አብራምና ሎጠ ተለያዩ። እግዚአብሔርም ለአብራምና ለቤተሰቡ በሁሉም አቅጣጫ የሚያየውን ምድር ሊያወርሰው ቃል ገባላት። (**ዘፍጥረት** 13: 14–18)<br>• *አብራምን ብትሆኑ ኖሮ ምን ይሰማችሁ ነበር? እንደተጭበረበራችሁ ሊሰማችሁ ይችላል? (ከሎጥ ምርጫ ይልቅ አብራም ከእግዚአብሔር ዘንድ የተቀበለው የተስፋ ቃል እንደሚበልጥ ንገሯቸው።)*<br>• *የሎጥ ምርጫ መጥፎ ምርጫ ነበር። በምናደርጋቸው ምርጫዎቻችን ብልሆች መሆን አለብን። ከምርጫዎች ሁሉ በላይ ኢየሱስ ክርስቶስን ወደ ሕይወታችን እንዲገባና ኃጢአታችንን ይቅር እንዲለን መጠየቅ ዋነኛው ነው።*<br>• *እግዚአብሔር ለእኛ የሚበጀንን ያውቃል። ልክ ለአብራም የሚሻውን ሁሉ ሊሰጠው እንደቻለ የእኛንም ፍላጎቶች ለማሟላት እንደሚችል በአንክሮ አስረዱ። እግዚአብሔር የተስፋ ቃሉን በመፈፀም ረገድ የሚታመን መሆኑን አስረዷቸው።*<br>**የዘመነ መጽሐፍ ቅዱስ ትምህርቶችን አጠናቁ።** |
| የመማር ጊዜ | ከሁለት አንደኛውን ቁልፍ ጥቅስ በመምረጥ አስተምሩ እንዲሁም አብራሩ። **ዘፍጥረት** 13:15 **ወይንም ፊልጵስዩስ** 4:19, ይህን ስታደርጉም ልጆች ቀደም ብሎ ከሰሙት ታሪክ ጋር አገናኙት። |
| የክለሳ ጊዜ | ይህ ታሪክ የሚጠናቀቀው አብራም መሰዊያ ሲገነባ በማሳየት ነው። በቡድኑ ውስጥ ጥያቄዎችን በአግባቡ መመለስ የሚችል ሰው ብዙ ጠጠሮችን መሰብሰብ እንዲችል ዳይስ መወርወር ***(dice)*** ይችላል። (**ዘፍጥረት** 13: 1–6) እውነተኛ ጠጠሮችን ወይንም ደግሞ ስዕሎችን መጠቀም ይቻላል። አሸናፊው ቡድን ብዙ ጠጠሮች ያሉት መሰዊያ ይኖረዋል።<br>• አብራም ባለፀጋ ሰው መሆኑን የምናውቀው እንዴት ነው?<br>• ግጭቱ መቆም አለበት ብሎ ሀሳብ ያቀረበው ማን ነበር?<br>• የመጀመሪያው መራጭ ማን ነበር?<br>• ሎጥ ሊያየው የቻለው ወንዝ የትኛውን ነበር?<br>• ሎጥ የተጓዘበት አቅጣጫ የትኛው ነበር?<br>• ሎጥ ስለ መረጠው ቦታ ጥሩ ያልሆነው ነገር ምን ነበር?<br>• እግዚአብሔር አብራምን ምን እንዲያይ ጠየቀው?<br>• አብራም ለቤተሰቡና ለእርሱ የሰጣቸው የተስፋ ቃል ምን ነበር?<br>• አብራም በሰራው መሰዊያ ላይ ምን አደረገ?<br>• በሕይወታችን ልናደርገው የምንችለው የመጨረሻው መልካም ምርጫ ምንድነው? |

## <u>ሀ5 ታሪክ 3</u>

## እግዚአብሔር ለአብራም የተስፋ ቃል ሰጠው – ይህ ታሪክ የእግዚአብሔርን የተስፋ ቃሎች ስለ ማመን የሚያስተምር ታሪክ ነው።

**በዚህ ክፍል የምንማራቸው የሚከተሉትን ነው።**

- እግዚአብሔር ወደፊት ምን ሊሆን እንደሚችል ስለ ሚያውቅ የተስፋ ቃሉን ሊሰጠን ይችላል።
- እግዚአብሔር ተስፋ ቃሎቹን እንድናምናቸው ይፈልጋል።

**ቁልፍ ጥቅስ** 1 **ቆሮንቶስ** 10: 13 **ወይንም ዘፍጥረት** 15: 6
**የጥናት ክፍል: ዘፍጥረት** 15: 1-7

### መግቢያ

- ለልጆች ሊደረግ የሚችል ቃል ኪዳን ምሳሌ ስጧቸው። ቃል ኪዳኑ እስኪፈፀም ድረስ በትዕግስት ሲጠብቁ ሊኖራቸው ስለ ሚገባ እምነትና የተስፋ ቃሉን ፍፃሜ በማሰብ በውስጣቸው ሊፈጠር ስለ ሚችል የደስታ ስሜት በአንክሮ ንገሯቸው። (እንዲሁም በሁኔታዎች ምክንያት ሊፈፀም ያልቻለ ቃል ኪዳን ምሳሌን መስጠት ትችላላችሁ።)
- ሰዎች የገቡትን ቃል ለመፈፀም ሊቸገሩ ይችላሉ። እግዚአብሔር ግን ሁሌም ቃል ኪዳኑን የሚፈፅም አምላክ ነው።

### የማስተማር ጊዜ

- እግዚአብሔር ለአብራም በሕልም ተገልጦ ወንድ ልጅ እንደሚሰጠው ቃል ኪዳን ገባለት።. (**ዘፍጥረት** 15: 1, 4) *ይህን እግዚአብሔር አስቀድሞ ለአብራም ከሰጣቸው የተስፋ ቃላት ጋር አዛምዱት። አሁን እድሜው ዘጠና አመት ለሆነው ለአብራም ይህ ዜና እንዴት አስደናቂ ዜና እንደሆነ ንገሯቸው።*
- እግዚአብሔር ለአብራም ከዋክብትን አሳይቶ ዘሩ ልክ እንደከዋክብቱ ብዙ እንደሚሆን ነገረው! (**ዘፍጥረት** 15: 5) *ከዋክብትን መቁጠር እጅግ ከባድ መሆኑን እንዲያስቡ ጠይቋቸው! ልጆች ከዋክብትንና የፈጠራቸውን አምላክ እያሰቡ እንዲያደንቁ አድርጓቸው።*
- አብራም እግዚአብሔር የሰጠውን የተስፋ ቃል አመነ። (**ዘፍጥረት** 15: 6) *አብራም እግዚአብሔርን ለምን እንዳመነ ምክንያቶቹን ዘርዝሩ።*
- እግዚአብሔር ለአብራምና ለሦራ አዲስ ስም ሰጣቸው። (**ዘፍጥረት** 17: 5, 15) *የአብርሃም አዲሱ ስሙ "የብዙዎች አባት" ማለት ነው። ይህም እግዚአብሔር የሰጠውን የተስፋ ቃል ሁልጊዜ እንዲያስብ ያደርገዋል።*
- *እግዚአብሔር በቃሉ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ለእኛ የተስፋ ቃላት ሰጥቶናል። በእግዚአብሔር ስንታመን ለእኛ የሆኑ ብዙ የተስፋ ቃላት አሉ። ለዚህ ምሳሌዎችን ስጧቸው።*
- *እግዚአብሔር የተናገረውን የተስፋ ቃል ስናምን እግዚአብሔር ደስ ይሰኛል።*

**የዘመነ መጽሐፍ ቅዱስ ትምህርቶችን አጠናቁ።**

### የመማር ጊዜ

ከሁለት አንደኛውን ቁልፍ ጥቅስ በመምረጥ አስተምሩ እንዲሁም አብራሩ። - 1 **ቆሮንቶስ** 10: 13 (እግዚአብሔር ታማኝ ነው።) – እግዚአብሔር ታማኝ ነው ስንል ቃል ኪዳኑን ለመፈፀም የሚችልና ልንታመንበት የሚገባ ነው ማለት ነው። ወይንም **ዘፍጥረት** 15: 6 – አብራም በእግዚአብሔር ሲታመን እግዚአብሔር እንደተደሰተ አስረዷቸው።

### የክለሳ ጊዜ

- እግዚአብሔር ለአብራም በገባለት የተስፋ ቃል አብራም የምን አባት እንደሚሆን ነው ቃል የገባለት?
- እግዚአብሔር በሕልም ወይንም በመገለጥ ለአብራም የሰጠው የተስፋ ቃል ምን ነበር?
- የአብራም ሚስት ማን ነበረች?
- እግዚአብሔር ለአብራም ያሳየው ምንድ ነበር?
- እግዚአብሔር ከዋክብትን ከምን ጋር ያወዳደራቸው ነበር?
- እግዚአብሔር ይህን የተስፋ ቃል ለአብራም ሲሰጥ አብራም ምን አደረገ?
- የአብራም አዲሱ ስሙ ማን ነበር?
- የሦራ አዲሱ ስሟ ማን ነበር?
- እግዚአብሔር ለእኛ የሰጠንን የተስፋ ቃላት ስናውቅ ምን እንድናደርግ ይፈልጋል?
- "ማመን" የሚለው ቃል እንዴት ይተረጎማል?

## <u>ሀ5 ታሪክ 4</u>

## አብርሃምና እንግዶች – ይህ ታሪክ የእግዚአብሔር የተስፋ ቃላት ፍፃሜን ይተርካል።

**በዚህ ክፍል የምንማራቸው የሚከተሉትን ነው።**

- እግዚአብሔር መልእክቶቹን በተለያየ መንገድ ይልካል። በተለይ ደግሞ መጽሐፍ ቅዱስ በፅሑፍ መልክ በሰዎች እጅ ከመግባቱ በፊት! ይህን መልዕክት ከእግዚአብሔር ወደ አብርሃም ይዘው የመጡት ሶስት ልዩ መልዕክተኞች ናቸው።
- እግዚአብሔር ለሰጠን የተስፋ ቃል ፍፃሜ ታማኝ ነው። ለእርሱ የሚከብደው አንዳችም ነገር የለም።

**ቁልፍ ጥቅስ** **ዘፍጥረት** 18: 14
**የጥናት ክፍል:** **ዘፍጥረት** 18: 1–15

### *መግቢያ*

- *ያልተጠበቁ እንግዶች ሲመጡባችሁ በባሕላችሁ ምን እንደሚደረግ ተነጋገሩ። ይህን ለማስረዳት የተለያዩ ቁሳቁሶችን ተጠቀሙ። ወይንም ደግሞ እንግዶችን በመቀበል ዙሪያ የሚና ጨዋታ ድራማ አዘጋጁ።.*
- *የአብርሃም እንግዶች ሲመጡ የሚያሳይ ትዕይንት አዘጋጁ። እንግዶቹ በእኩለ ቀን ወደ አብርሃም ድንኳን እየተቃረቡ ሳለ አብርሃም በድንኳኑ ደጅ ላይ ተቀምጦ አረፍ ብሏል። እንግዶቹ እነማን ሊሆኑ ይችላሉ?*

### የማስተማር ጊዜ

- አብርሃም ለእንግዶቹ አቀባበል አደረገላቸው። ውኃና ምግብም አቀረበላቸው። (**ዘፍጥረት** 18: 2–8) *የሳራን ድርሻ አብራሩ። ይህን ታሪክ ስትተርኩ ትዕይንቶችን አብራችሁ አሳዩ። ብሩህ ሰማይ፣ እግራቸውን እየታጠቡበት ያለውን ውኃ፣ የምግቡን ሽታ ወዘተ...*
- እንግዶቹ ከተመገቡ በኋላ ሳራ በሚቀጥለው አመት ወንድ ልጅ እንደምትወልድ ለአብርሃም ነገሩት። (**ዘፍጥረት** 18: 9, 10) *እንግዶቹ ይህን እንዴት ማወቅ ይችላሉ? ጎብኝዎቹ ማን እንደሆኑ አብራሩላቸው። ከእግዚአብሔር ዘንድ ከሰማይ የመጡ መልእክተኞች ናቸው። አንደኛው ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ሲሆን ሌሎቹ ደግሞ መላእክት ናቸው። አብርሃም ይህን ዜና ሲያበስሩት ምን ሊሰማው እንደሚችል ተወያዩ። የእግዚአብሔር የተስፋ ቃላት ለፍፃሜ እየተቃረቡ ነበር!*
- *ሳራ ሳቀች። ምክንያቱም ይህ በፍፁም የማይሆን ነገር እንደሆነ ስላሰበች ነው። ሆኖም በእግዚአብሔር ዘንድ የማይቻል ከቶ አንዳችም ነገር የለም!* (**ዘፍጥረት** 18: 11–15 ) *ሳራ ስትስቅ እግዚአብሔር ምን ሊሰማው እንደሚችል ተወያዩ።*
- ከአንድ አመት በኋላ ሳራ ልጅ ወለደች። (**ዘፍጥረት** 21: 1–7) *በዚህ ምክንያት በቤተሰቡ ውስጥ የተፈጠረውን የደስታ ስሜት አስቡ። እግዚአብሔር ቃል ኪዳኑን መፈፀም ቻለ? ከደረጃ 2 ተማሪዎች ጋር የይስሐቅ ስም ትርጉሙ ምን እንደሆነ ማውራት ትችላላችሁ። (ሳቅ)*
- *እግዚአብሔር ለእኛ የገባቸውን ቃላት በመፈፀም ረገድ ሊታመን ይገባዋል። የሚከብደው አንዳችም ነገር የለም። – ዛሬም ልክ እንደቀድሞው ታማኝ ነው! የምናመልከው አምላክ ምንኛ ድንቅ ነው!*

**የዘመነ መጽሐፍ ቅዱስ ትምህርቶችን አጠናቁ።**

### የትምህርት ጊዜ

ቁልፍ ጥቅሱን እያብራራችሁ አስተምሩት። - **ዘፍጥረት** 18: 14

### የክለሳ ጊዜ

ከዚህ በታች የቀረቡት የሙከራ ጥያቄዎች ከዚህ ታሪክ ጋር የተዛመዱ ናቸው። እነኝህን ጥያቄዎች መጠቀም ትችላላችሁ። ወይንም ደግሞ በሀ 5 ውስጥ ባሉት አራት ታሪኮች ውስጥ ካሉት ጥያቄዎች በማውጣጣት መጠቀም ትችላላችሁ።

- እንግዶቹ የመጡት በምን ሰዓት ነበር?
- አብርሃም እንግዶቹ ሲመጡ የት ነበር?
- አብርሃም ሳራን ምን እንድታደርግ አዘዛት?
- በተጨማሪ ምን መብላት ነበረባቸው?
- መልእክተኞቹ መልካሙን ዜና ሲናገሩ ሳራ የት ነበረች?
- ሳራ ለምን ሳቀች?
- ዜናውን ከሰማች በኋላ ሳራ ልጅ ለመውለድ ምን ያህል ጊዜ መጠበቅ ነበረባት?
- የወለደችው ልጅ ስሙ ማን ነበር?
- ይስሐቅ ሲወለድ የአብርሃም እድሜ ምን ያህል ነበር?
- አብርሃምና ሳራ የሚደሰቱባቸውን ሁለት ምክንያቶች አስቡ። (ልጅ አገኙ። እግዚአብሔር ለእነርሱ የገባውን የተስፋ ቃል ፈፀመ።)

**ተውኑት**: ልጆች የዚህ ታሪክ መጀመሪያ ክፍል ሲተወን ሲያዩ በጣም ደስ ያሰኛቸዋል። ሁሉንም ተግባራት በአላማ አድርጓቸው። በፈቃደኝነት የሚያግዙ አዋቂዎች የአብርሃምን፣ የሳራንና የሶስቱን ጎብኚዎች ገፀ ባሕርያት ይጫወቱ። በአማራጭ በትንንሽ ቡድኖች ውስጥ ሆነው የገፀ ባሕርያትን ንግግሮች ከተከፋፈሉ በኋላ በአካላዊ እንቅስቃሴ አጅበው መናገር ይችላሉ።

## ሀ6 ታሪክ 1

## አብርሃም እግዚአብሔርን ሰማ። – ይህ ታሪክ እግዚአብሔርን መውደድ ከሁሉም እንደሚበልጥ ይናገራል።

| | |
|---|---|
| | **በዚህ ክፍል የምንማራቸው የሚከተሉትን ነው፡፡**<br>• አብርሃም እግዚአብሔርን ከምንምና ከማንም በላይ አብልጦ ወደደ።<br>እኛም እግዚአብሔርን በሙሉ ልባችን መውደድ አለብን።<br>**ቁልፍ ጥቅስ** **ዘፍጥረት** 22: 8 **ወይንም** **ዘዳግም** 6: 5<br>**የጥናት ክፍል:** **ዘፍጥረት** 22: 1-9 |
| *መግቢያ* | • ልጆች ለእነርሱ እጅግ በጣም አስፈላጊ ናቸው የሚሏቸውን ነገሮች እንዲነግሯችሁ ጠይቋቸው። – በሕይወታችሁ በጣም አስፈላጊ ነገር ምንድነው? ለምን አስፈላጊ ሆነ?<br>• ከዚያም ይህ እጅግ በጣም አስፈላጊ ነው የሚሉት ነገራቸው ቢወሰድባቸው ምን ሊሰማቸው እንደሚችል ጠይቋቸው። ያን ነገር ለማጣት ፈቃደኞች ይሆናሉ? ቢወሰድባቸውስ ምን ይሰማቸዋል? የዛሬው ታሪክ ለአብርሃም እጅግ በጣም ልዩና አስፈላጊ የሆነውን ነገር አሳልፎ እንዲሰጥ ጥያቄ እንደቀረበለት የሚተርክ እንደሆነ አስረዷቸው። |
| *የማስተማር ጊዜ* | • እግዚአብሔር ለአብርሃምና ለሳራ ልጅ ሊሰጣቸው የገባላቸውን ተስፋ ፈፀመ። ስሙ ይስሐቅ ይባላል። እጅግ በጣም ይወዱት ነበር። (**ዘፍጥረት** 21: 1-3)<br>• አንድ ቀን እግዚአብሔር አብርሃምን ልጁን ይስሐቅ ወደ ሞሪያም ተራራ ይዞ እንዲሄድ ጠየቀው። በዚህን ወቅት ምናልባት ይስሐቅ በለጋ የወጣትነት እድሜ ውስጥ ሊሆን ይችላል። እግዚአብሔር አብርሃም ልጁን ይስሐቅን መስዋዕት አድርጎ እንዲሰጠው ፈለገ። እግዚአብሔር አብርሃምን ይወደው እንደሆነ ለመፈተን ይህን አደረገ። ይህ ነገር አብርሃምን ቢያሳዝነውም እግዚአብሔርን አምኖ እግዚአብሔር የጠየቀውን ነገር አደረገ። (**ዘፍጥረት** 22: 1-2) *አብርሃም እግዚአብሔርን ከልቡ ያፈቅር ነበር። ምንም እንኳን ይህ ጥያቄ ከባድ ቢሆንም እግዚአብሔርን ሰምቶ ለመታዘዝ ፈቃደኛ ነበር።*<br>• ጥዋት በማለዳ አብርሃም ለመስዋዕት የሚያስፈልገውን እንጨት ፈለጠ። በአህዮች ላይም ጫነው። ለጉዞው የሚያስፈልጉ ሌሎች ነገሮችንም አዘጋጀ። ሁለት ሎሌዎቹንም ከእርሱ ጋር ይዞ ጉዞ ጀመረ። (**ዘፍጥረት** 22: 3)<br>• ከሶስት ቀናት በኋላ እግዚአብሔር ወደ መረጠው ተራራ መጡ። አብርሃም ሁለቱን ሎሌዎቹንና አህዮቹን ትቷቸው ሄደ። ይስሐቅ የመስዋዕቱን እንጨት ተሸከመ። አብርሃም ደግሞ ካራውንና እሳቱን ያዘ። (**ዘፍጥረት** 22: 4-6)<br>• ተራራውን በመውጣት ላይ ሳሉም ይስሐቅ አባቱን የመስዋዕቱ በግ የት እንዳለ ጠየቀው። አብርሃምም "ልጄ የመስዋዕቱን በግ እግዚአብሔር ያዘጋጃል"። ብሎ መለሰለት። (**ዘፍጥረት** 22: 7-8)<br>• *አብርሃም እግዚአብሔርን ስለ ሚያፈቅረው ታዘዘው። እግዚአብሔር እኛም በሙሉ ልባችን ልናፈቅረውና እንድናደርግ የሚጠይቀንን ሁሉ ልንታዘዘው ይገባል።*<br><br>**የዘመኑ መጽሐፍ ቅዱስ ትምህርቶችን አጠናቁ።** |
| *የመማር ጊዜ* | እንደአስፈላጊነቱ የመጽሐፍ ቅዱስ ቁልፍ ጥቅሶችን አብራሩ፣ አስተምሩ። - **ዘፍጥረት** 22: 8 **ወይንም** **ዘዳግም** 6: 5 |
| *የክለሳ ጊዜ* | • የአብርሃም ልጅ ስሙ ማን ነበር?<br>• እግዚአብሔር አብርሃም ወደ የትኛው ተራራ እንዲሄድ ነው ያዘዘው?<br>• አብርሃም ከእርሱ ጋር ስንት ሎሌዎችን ይዞ ሄደ?<br>• አብርሃም ከእርሱ ጋር ይዞ የሄደው ምን አይነት እንስሳ ነበር?<br>• ወደ ተራራው ለመድረስ ምን ያህል ጊዜ ፈጀባቸው?<br>• አብርሃም "የመስዋዕቱን በግ" የሚያዘጋጀው ማን ነው አለ?<br>• አብርሃም ከምንምና ከማንም በላይ አብልጦ የሚወደው ማንን ነበር?<br>• በሙሉ ልባችን መውደድ ያለብን ማንን ነው? |

## ሀ6 ታሪክ 2

## አብርሃም እግዚአብሔርን ታዘዘ። – ይህ ታሪክ የይስሐቅ ምትክ ስለ ሆነው የመስዋዕት በግ ይናገራል።

| | |
|---|---|
| | **በዚህ ክፍል የምንማራቸው የሚከተሉትን ነው።**<br>• እግዚአብሔር የይስሐቅ ምትክ የሚሆነውን የመስዋዕት በግ አዘጋጀ።<br>• ኢየሱስ በእኛ ኃጢአት ምክንያት በመስቀል ላይ ሲሞት የእኛ ምትክ ሆነ።<br>**ቁልፍ ጥቅስ** **ገላትያ 2: 20**<br>**የጥናት ክፍል:** **ዘፍጥረት 22: 9-14** |
| *መግቢያ* | • ልጆች ባጠፉት አንድ ጥፋት ምክንያት ሊቀጡ እንዳላቸው እንዲያስቡ አድርጓቸው። – ምን ይሰማችኋል?<br>• ከዚያም አንድ ሰው ይመጣና በእነርሱ ምትክ ይቀጣላቸዋል። በዚህን ጊዜስ ምን ይሰማቸዋል?<br>• የዛሬው ትምህርት የይስሐቅ ምትክ ስለ ሆነ ነገር የሚማሩበት ትምህርት እንደሆነ ለልጆች አስረዷቸው። |
| የማስተማር ጊዜ | የእስካሁኑን ታሪክ ልጆች እንዲያስታውሱት አድርጓቸው።<br>• በመጨረሻም አብርሃምና ይስሐቅ ወደ ተራራው ጫፍ ደረሱ። በድንጋይ መሰዊያ ሰሩ። ይስሐቅም በመሰዊያው ላይ ተጋደመ። (**ዘፍጥረት 22: 9-10**)<br>• አብርሃም ይስሐቅን ሊሰዋው ሲቃረብ ከሰማይ አንድ መልአክ ጠርቶ ልጁን እንዳይጎዳው አዘዘው። አሁን አብርሃም እግዚአብሔርን ምን ያህል እንደሚወደው አሳየ። (**ዘፍጥረት 22: 11-12**)<br>• አብርሃም ቀና ብሎ ሲመለከት በቁጥቋጦ መካከል በቀንዱ የተያዘ በግ አየ። በይስሐቅ ምትክም በጉን በመሰዊያ ላይ አጋደመው። (**ዘፍጥረት 22: 13**)<br>• *የመስዋዕቱ በግ በይስሐቅ ምትክ እንደሚሰዋ ሲያውቁ አብርሃምና ይስሐቅ ሊሰማቸው የሚችለው ምንድነው ትላላችሁ?*<br>• *ኢየሱስ በመስቀል ላይ ሲሞት የእኛን ቦታ ወሰደ። ሁላችንም ኃጢአትን አድርገናል። ለዚህ ኃጢአታችን የሚገባንን ቅጣትም ኢየሱስ ተቀጣልን።*<br>• *ኢየሱስ ስለ እኛ የሞተው ስለወደደንና በኃጢአታችን ምክንያት ስንቀጣ የሚደርስብንን ስቃይ ስለ ማይፈልግ ነው።*<br>• *እኛም እንድንወደውና ስላደረገልን እንድናመሰግነው ይፈልጋል።*<br>• *ኢየሱስ እጅግ በጣም ስለ ወደዳችሁ ስለ እናንተ መሞቱን ስትረዱ ምን ይሰማችኋል?*<br>*ለኢየሱስ ያለንን ፍቅር የምንገልፀው እንዴት ነው?*<br>**የዘመኑ መጽሐፍ ቅዱስ ትምህርቶችን አጠናቁ።** |
| *የመማር ጊዜ* | እንደአስፈላጊነቱ የመጽሐፍ ቅዱስ ቁልፍ ጥቅሶችን አብራሩ፣ አስተምሩ። - **ገላትያ 2: 20** |
| የክለሳ ጊዜ | • አብርሃም የሰራው መሰዊያ የት ነበር የሚገኘው?<br>• መሰዊያውን ለመስራት የተጠቀሙት ምን ነበር?<br>• ከሰማይ የተጣራው ማን ነበር?<br>• መልአኩ አብርሃም ምን እንዲያደርግ አዘዘው?<br>• አብርሃም ለእግዚአብሔር ያሳየው ምን ነበር?<br>• በመሰዊያው ላይ የይስሐቅ ምትክ የሆነው ምን ነበር?<br>• በመስቀል ላይ የእኛን ቦታ የወሰደው ማን ነበር?<br>• ኢየሱስ በመስቀል ላይ የሞተው ለምን ነበር? |

## ሀ6 ታሪክ 3
## እግዚአብሔር ይረዳል – ይህ ታሪክ  እግዚአብሔር መንገድን እንዴት እንደሚያሳይ ይተርካል።

**በዚህ ክፍል የምንማራቸው  የሚከተሉትን ነው።**

- አገልጋዩ ከእግዚአብሔር ዘንድ እርዳታን ለመነ። እግዚአብሔርም ረዳው።
- እኛም ብንለምነው እግዚአብሔር ይረዳናል።

**ቁልፍ ጥቅስ** **ዘፍጥረት  24: 27 ወይንም ማቴዎስ  7: 7**
**የጥናት ክፍል:** **ዘፍጥረት  24: 1-28**

### መግቢያ

- ልጆች ስለ ሚረዷቸው ሰዎች እንዲያስቡ ጠይቋቸው። – የሚረዳችሁ ማነው? በምን አይነት ጉዳዮች ነው የሚረዷችሁ? ሲረዷችሁ ምን ስሜት ይሰማችኋል?
- ልጆች ሌሎች ሰዎችን የረዱባቸውን አጋጣሚዎች እንዲናገሩ ፍቀዱላቸው።
- የዛሬው ታሪክ እግዚአብሔር አንድን ሰው እንዴት እንደረዳ እንደሚናገር ለልጆቹ ንገሯቸው።

### የማስተማር ጊዜ

- አብርሃም እጅግ አርጅቶ ነበር። ሆኖም ከመሞቱ በፊት ይስሐቅ እንዲያገባና በትዳሩም ደስተኛ እንዲሆን ይፈልግ ነበር። ስለዚህም ሎሌውን ጠርቶ ለይስሐቅ ሚስት እንዲፈልግለት መመሪያዎች ይሰጠዋል። ትክክለኛዋን ሴት በመምረጥ ረገድ በእግዚአብሔር እንዲታመን ይነግረዋል። (**ዘፍጥረት** 24: 1-9) *የአብርሃም ሎሌ ለይስሐቅ ሚስት እንዲፈልግለት ሲታዘዝ ምን ሊሰማው ይችላል?*
- ሎሌው የአብርሃምን አስር ግመሎች ይዞ ጉዞ ጀመረ።  ለረዥም ቀናት ከተጓዘ በኋላ በናኮር ከተማ በአንድ የውሃ ጉድጓድ አጠገብ ቆመ። ቀኑ አመሻሽ ነበር። ስለዚህም የከተማይቱ ልጃገረዶች ውኃ ለመቅዳት ወደ ጉድጓዱ መምጣት ጀመሩ። (**ዘፍጥረት**  24: 10-11)
- ሎሌውም አሁን ወደ ውኃ ጉድጓዱ እየመጡ ካሉት ልጃገረዶች መካከል  ለጌታው ለይስሐቅ የምትሆነውን ሚስት እንዲያሳየው ወደ እግዚአብሔር ፀለየ። ምልክቱም ውኃ አጠጪኝ የሚላት ልጃገረድ ለእርሱና ለአስሩ ግመሎቹ የሚጠጣ ውኃ የምታቀርብለት እርሷ እግዚአብሔር ለጌታው ለይስሐቅ ሚስት እንድትሆን እንደመረጣት ያውቃል። (**ዘፍጥረት**  24: 12-14)
- ወዲያው አንዲት ውብ ልጃገረድ እርሱ ወዳለበት የውኃ ጉድጓድ ስትመጣ አያት። ስሟ ርብቃ ይባላል። የሚጠጣ ውኃ ሲጠይቃት በደስታ የሚጠጣ ውኃ ሰጠችው። እንደውም ለግመሎቹ የሚበቃ የሚጠጣ ውኃም ጨምራ ሰጠችው። *አሁን ሎሌው ምን ሊያስብ ይችላል? ምንስ ይሰማዋል?* (**ዘፍጥረት**  24: 15-21)
- ከጌታው ከአብርሃም ያመጣውን ስጦታ ከሰጣት በኋላ በመኖሪያቸው ለእርሱና ለግመሎቹ ሌሊቱን የሚያሳልፉበት ቦታ ማግኘት ይችሉ እንደሆነ ጠየቃት።  ብዙ ቦታ እንዳለ ስትነግረው በግንባሩ ወደ መሬት ተደፍቶ ሰገደ። እግዚአብሔርም ፀሎቱን ስለ መለሰና ትክክለኛዋን የይስሐቅን ሚስት እንዲያገኛት ስለ ረዳው አመሰገነ። (**ዘፍጥረት**  24: 22-27)
- *አስቸጋሪ የሆነ ኃላፊነት ተሰጥቷችሁ ያውቃል? አግባብነት ያላቸው ምሳሌዎችን አቅርቡላቸው።*
- *ሎሌው እርዳታ የጠየቀው ከማን ነበር?*
- *እንዲረዳን መጠየቅ ያለብን ማንን ነው? አስቸጋሪ አማራጮች ከፊታችን ድቅን ሲሉና መወሰን ሲከብደን እግዚአብሔር እንዲረዳን እንድንጠይቀው ይፈልጋል። ትክክለኛውን ምርጫ እንድንመርጥም እግዚአብሔር ይረዳናል።*

**የዘመነ መጽሐፍ ቅዱስ ትምህርቶችን አጠናቁ።**

### የመማር ጊዜ

እንደአስፈላጊነቱ የመጽሐፍ ቅዱስ ቁልፍ ጥቅሶችን አብራሩ፣ አስተምሩ። - **ዘፍጥረት  24: 27 ወይንም ማቴዎስ  7: 7**

### የክለሳ ጊዜ

- ለይስሐቅ ሚስት ሊፈልግለት የሄደው ማን ነበር?
- ሎሌው ከእርሱ ጋር ስንት ግመሎችን ይዞ ሄደ?
- ሎሌው የቆመው የት ነበር?
- ይህ ስንት ሰአት ላይ ነበር?
- ለይስሐቅ የምትሆነውን ትክክለኛዋን ሚስት ማግኘት እንዲችል እርዳታ የጠየቀው ማንን ነበር?
- በውኃ ጉድጓዱ አጠገብ የነበረችው ልጃገረድ ስሟ ማን ነበር?
- ሎሌውን ለመርዳት ምን አደረገች?
- እግዚአብሔር እንደረዳው ሲያውቅ ሎሌው ምን አደረገ?

ጊዜው የሚፈቅድ ከሆነ ልጆች ሰው ሲረዱ የሚያሳይ ስዕል እንዲሰሩ ጠይቋቸው።

## <u>ሀ6 ታሪክ 4</u>

## የእግዚአብሔር ምርጫ – ይህ ታሪክ ስለ ይስሐቅና ስለ ርብቃ ጋብቻ ያወሳል።

**በዚህ ክፍል የምንማራቸው የሚከተሉትን ነው።**

- ርብቃና ይስሐቅ የእግዚአብሔርን እቅድ ተከተሉ። ስለዚህም ደስተኞች ናቸው።
- የእግዚአብሔርን መንገድ ስንከተልና በእግዚአብሔር ስንታመን ደስተኞች እንሆናለን። .

**ቁልፍ ጥቅስ** ***መዝሙረ ዳዊት*** **144: 15**
**የጥናት ክፍል:** **ዘፍጥረት 24: 28-67**

### *መግቢያ*

- ልጆች ሰርግ ቦታ ተጋብዘው ሄደው እንደሆነ ጠይቋቸው። ያገባው ማን ነበር? የለበሱት ምን ነበር? በሰርጉ ቦታ ምን ተከናወነ? ሙሽሮቹ ደስተኞች ነበሩ?
- የዛሬው ታሪክ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ስለ ተከናወነ የሰርግ ስርአት የሚያወሳ ታሪክ እንደሆነ ለልጆች ንገሯቸው። ምናልባትም ይህ ታሪክ በአካባቢያችሁ ከምታውቋቸው የሰርግ አይነቶች የተለየ ሊሆን ይችላል።

### የማስተማር ጊዜ

- እስካሁን ድረስ ያያችኋቸውን ታሪኮች ልጆች እንዲያስታውሱ አድርጓቸው።
- ርብቃ የሆነውን ነገር ለመንገር ወደ ቤት እየሮጠች ሄደች። ወንድሟ ላባም ይህን ሲሰማ እየሮጠ ወደ ውኃው ጉድጓድ ሄደ። የአብርሃምን ሎሌ ወደ ቤት ይዘውት መጡ። አቀባበልም አደረጉለት። ሆኖም እራት ከመቅረቡ በፊት የመጣበትን ምክንያት ለርብቃ ቤተሰብ አስረዳ። (**ዘፍጥረት** 24: 28-49)
- የርብቃ አባትና አጎቷ ላባ የአብርሃምን ሎሌ እግዚአብሔር ወደዚህ ቤተሰብ መርቶ እንደላከው እርግጠኞች ነበሩ። ያለምንም ጥርጥር ርብቃን ከእርሱ ጋር ይዟት እንዲሄድና ለይስሐቅ ሚስት እንድትሆነው ተስማሙ። የአብርሃም ሌሎም እግዚአብሔር ፀሎቱን ስለ መለሰለት እግዚአብሔርን አመሰገነው። ስለዚህም በርካታ ስጦታ ለርብቃና ለቤተሰቦቿ ሰጣቸው። (**ዘፍጥረት 24: 50-53**)
- በነጋታውም ርብቃ ተጠርታ ከአብርሃም ሎሌ ጋር አብራ መሄድና ይስሐቅን ማግባት ፍላጎቷ እንደሆነ ተጠየቀች። ርብቃም ለመሄድ ተስማማች። (**ዘፍጥረት 24:** 54-61) *ርብቃ ምን የሚሰማት ይመስላችኋል? (ፍርሃት ሊሰማት ይችላል። ምክንያቱም ይስሐቅንም ሆነ ቤተሰቦቹን አታውቃቸውም። ሆኖም ይህ የእግዚአብሔር ፈቃድ እንደሆነ እርግጠኛ ስለ ሆነች ደስተኛ ነበረች!)*
- በአብርሃም ቤት ደግሞ ይስሐቅ ምን ተፈጥሮ እንደሆነ ለማወቅ በጉጉት በመጠባበቅ ላይ ነው። አንድ ምሽት ላይ ይስሐቅ በሽርሽር ላይ ሆኖ ግመሎች ሲመጡ አየ። ወዲያውኑም ለርብቃ እንኳን ወደ አዲሱ ቤትሽ በደህና መጣሽ ሲል አቀባበል አደረገላት። ወደ እናቱ ድንኳንም አስገባት። ይስሐቅ ርብቃን እጅግ በጣም አፈቀራት። ሚስትም ሆነችው። (**ዘፍጥረት 24:** 61-67)
- *ይስሐቅ ሚስቱን ሲያያት ምን ስሜት የተሰማው ይመስላችኋል? (በጣም ደስተኛ ሊሆን ይችላል። ጥቂትም የመደናገጥና የፍርሃት ስሜትም ሊኖርበት ይችላል። ምክንያቱም ርብቃን አይቷት ስለ ማያውቅ። ሆኖም በእግዚአብሔር ፈቃድ ታመነ። ስለዚህም ርብቃን ሚስቱ አድርጎ ለመውሰድ ደስተኛ ነበር።)*
- *በእግዚአብሔር ስለ ታመኑና የእግዚአብሔርን ፈቃድ ስለ ተከተሉ ይስሐቅና ርብቃ ሁለቱም በጣም ደስተኞች ነበሩ። እግዚአብሔር በእርሱ እንድንታመንና ፈቃዱን እንድንከተል ይፈልጋል። ይህን ስናደርግ በደስታና በሐሴት እንሞላለን።*

**የዘመነ መጽሐፍ ቅዱስ ትምህርቶችን አጠናቁ።**

### የመማር ጊዜ

ቁልፍ ጥቅሱን እያብራራችሁ አስተምሩት። - ***መዝሙር*** 144: 15. ይህ ጥቅስ እግዚአብሔር ፈቃዱን በሕይወታችን ሲፈፅም ምንኛ ደስተኞች እንደምንሆን ያስረዳል።

### የክለሳ ጊዜ

- የርብቃ ወንድም ስሙ ማን ነበር?
- የአብርሃም ሎሌ እራት ከመብላቱ በፊት ምን አደረገ?
- የርብቃ ቤተሰብ ርብቃ ለይስሐቅ ሚስት እንድትሆነው የተስማሙት ለምን ነበር?
- የአብርሃም ሎሌ ለርብቃና ለቤተሰቧ ምን ሰጣቸው?
- የአብርሃምን ሎሌ ወደ ርብቃ የመራው ማን ነው አሉ?
- ርብቃ ከአብርሃም ሎሌ ጋር የሄደችው መቼ ነበር?
- ርብቃና የአብርሃም ሎሌ ሲመጡ በሽርሽር ላይ የነበረው ማን ነበር?
- ይስሐቅና ርብቃ በአንድ ላይ ደስተኛ የሆኑት ለምን ነበር?
- ከምንም ወይንም ከማንም በላይ ደስተኛ የሚደርገን ምንድነው?

# ለመምህራን የእርማት መመሪያ

**ለደረጃ 1 ትምህርቶች**

- በሳምንት አንድ ገፅ (ወይንም በእያንዳንዱ ጥራዝ ሁለት ገፆች) ይሰጣቸዋል። ይህም በዋነኝነት ቀለም መቀባትና የጎደሉ ቃላት መሙላትን ይይዛል።
- በየሳምንቱ 10 ነጥብ ይሰጣል። ወይንም በወር ቢበዛ 40 ነጥብ ብቻ ያገዝላቸዋል።
- የደረጃ 1 ተማሪዎች ብዙ እንዲያነቡ ስለ ማይጠበቁ ወላጆች/ሕጋዊ አሳዳጊዎች/ እንዲሁም መሪዎች እርዳታ እንዲሰጧቸው ይጠበቃል።
- ለአንድ መልስ ሁለት ነጥብ ይሰጣል። እንዲሁም በእያንዳንዱ ትምህርት ለቀለም ቅብ 10 ነጥብ ይሰጣል።

**ደረጃ 2 ትምህርቶች:**

- በሳምንት 2 ገፆች ወይንም ደግሞ በአንድ ጥራዝ 4 ገፆች ይሰጣቸዋል።
- ታሪኮቹ የሚገኙት በየትምህርቶቹ ውስጥ ነው። ተማሪዎች የተለያዩ ቃላትን ከየትምህርቶቹ መፈለግ፣ የቀለም ቅብ ስራ መስራትና ቁልፍ ጥቅሶችን ማሟላት ወዘተ... ይጠበቅባቸዋል።
- ልክ ትምህርቶቹ ሲጠናቀቁ በየሳምንቱ ሀያ ነጥቦ በወር ደግሞ ቢበዛ 80 ነጥቦች ሊሰጡ ይገባል።

**የዘመነ መጽሐፍ ቅዱስ ትምህርቶች ነጥብ አሞላል**

**የነጥብ አሞላል ፍንጮች**

*መምህራን በመጀመሪያ የሚከተሉትን እንዲያደርጉ ይጠየቃሉ።*

- እያንዳንዱን ትምህርት መገምገምና መልሶቹ ትክክል መሆን አለመኖናቸውን ምልክት ማድረግ።
- በመመሪያው መሰረት ትክክለኛውን ነጥብ መስጠት።
- ነጥብ ስንሰጥ የተለያየ አይነት ቀለም ያላቸውን ብዕሮች /እስክርቢቶዎች/ መጠቀም አለበን። ትክክል ለሆኑ መልሶች የ "✓" ምልክት እናድርግ።
- ትክክል ላልሆኑ መልሶች ትክክለኛ መልሶቻቸውን አስቀምጡ። የፊደላት ግድፈቶች ካሉም እርማት ስጡ። ለፊደላት ግድፈት ነጥብ አይቀነስም።
- በከፊል ትክክል ለሆኑ መልሶች ነጥብ ቀንሱ።
- የወሩን ድምር ነጥብ አስቀምጡ። ይህንንም በጀርባ ገፅ ለዚሁ ተብሎ በተዘጋጀው ክፍት ቦታ ለይ ፃፉ።

አንዳንዴ በአግባቡ ለጋስ መሆን ያስፈልጋል። እንዲሁም ተማሪዎች የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናቱን ማጠናቀቅ እንዲችሉ ለማበረታታት ማንኛውንም ነገር ማድረግ አስፈላጊ ነው። በየወሩ መጨረሻ መምህራን አንድ የማበረታቻ ቃል ለተማሪዎች ቢፅፉ መልካም ነው። ይህን ለማድረግም በየትምህርቶቹ ቦታ ተዘጋጅቷል። ጥሩ የቀለም ቅብን፣ ንፅሕናን፣ ተማሪው ያስመዘገበውን ነጥብ፣ ተማሪው ምን ያህል እንደተረዳ የሚገልፁ አስተያየቶችን መፃፍ ይቻላል።

አስተያየቶች በተቻለ መጠን የተለያዩ እንዲሆኑ መጣር አለብን። ጥያቄዎች፣ አረፍተ ነገሮች፣ ምልከታዎች፣ ማበረታቻዎች ወዘተ...ይህን ልዩነት ለማሳየት ልንጠቀምባቸው እንችላለን። ይህ በጥልቅ ማሰብንና የተማሪዎች ፍላጎት መጠበቁን ማረጋገጥ ይጠይቃል። አንድ አረፍተ ነገር ወይንም ደግሞ ጥያቄ በየወሩ የሚደጋገም ከሆነ የሚፈለገውን ግብ ላይመታ ይችላል።

**ደረጃ 1**

**አጠቃላይ አስተያየቶች**

> "ኤሚ ይህን ትምህርት በመጀረሽ በጣም ደስተኛ ነኝ። እንዲሁም በትምህርቶቹ በጣም ደሰተኛ እንደሆንሽ እርግጠኛ ነኝ። የቀለም ቅብሽ አስደስቶኛል። ትምህርት ቤት እየሄድሽ ነው ወይ? እስኪ ስለ ትምህርት ቤትሽ ንገሪኝ። መልስሽን በናፍቆት እጠብቃለሁ።"
>
> "እንድርያስ! እጅግ በጣም ግሩም ስራ ነው። የሚገርም ቅብ ነው! መስመር መጠበቅ ከባድ ነበር እንዴ? አንድ ቅብ ሊያርፍበት የሚገባውን ቦታ የዘነጋኸው አይመስልህም?"

***መንፈሳዊ አስተያየቶች***

> "ሳራ! ግሩም ስራ! ኢያኢሮስ ኢየሱስ የረዳው ደስተኛ ሰው ነበር!"
>
> "እጅግ በጣም ጥሩ መልሶች! የኢየሱስ ሞት ታሪኩ አሳዛኝ ቢሆንም ከሙታን መነሳቱ ደግሞ እጅግ አስደሳቹ ጫፍ ነው።"

**ደረጃ 2**

**አጠቃላይ አስተያየቶች**

" ዮናስ፣ መልስህ ጥሩ ነው። እርግጠኛ ነኝ የት/ቤት አስተማሪዎችህ በአንተ እጅግ በጣም ደስተኞች እንደሆኑ እርግጠኛ ነኝ።"

"ብሩክ! የልደት ቀንህ እየደረሰ እንደሆነ አውቄአለሁ። ለልደትህ ልዩ ዝግጅት እያደረግህ ነው? ምንም ነገር ብታደርግ መልካም ልደት እመኝልሃለሁ።"

"ጥረትህ በጣም አስገራሚ ጥረት ነው። ትንንሽዬ ስህተቶች አሉ። ሁልጊዜም መልሶችህን እንደገና አረጋግጥ።

**መንፈሳዊ አስተያየቶች**

"በበረት ውስጥ ያለውን ሕፃኑን ኢየሱስን የቀባሸበት መንገድ አስደስቶኛል። እግዚአብሔር ልጁን ወደ ዓለም ስለ እኛ መላኩ መልካም አይደለምን?

"ቅቦችህን በጣም ወድጃቸዋለሁ! እግዚአብሔር ያለውን ነገር ባለማመኑ ዘካሪያስን ዋጋ አስከፈለው። ከዚያ በኋላ የእግዚአብሔርን ቃል አልተጠራጠረም።"

"እጅግ በጣም አስደናቂ መልሶች! በምድረ በዳ ፊልጶስን የተገናኘው ሰው ደስተኛ ሆኖ ሄደ። ስለ ኢየሱስ መልካሙን ዜና ሰምቶ አመነ።

bible educational services

© የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርቶች አገልግሎት 2007ዓ.ም.

www.besweb.com

በሕግ የተመዘገበ የዩ.ኬ ሊጋሽ ድርጅት 1096157